መከላከያቸው ተአማኒነት እንዳይኖራቸው አድርጓታል:: የጋራ ምስክሮች ራሳቸውም ቢሆን በአንድ በኩል ሁሉም የመንግስት ሰራተኞች እና ታጣቂዎች በግቢው እንዳደሩ እየመሰከሩ በሌላ በኩል ተከሳሾች አልነበሩም:: ማለታቸውን የጥናት ምስክሮች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው:: 8ኛ ተከሳሽ የሚች ልጅ ተስፋይ ገ/ሄር የተባለ በአባቴ ግድያ አንተ እጅህ እንደሌለበት አውቃለሁ አንተን የፈለግኩህ ግን በምስክርነት እንድትረዳኝ ነው ብሎኝ ነበር በማለት ያቀረበውም የሚች ልጅ በወቅቱ በቦታው ስለነበረ ነው ይህ ዓይነት ጥያቄ ያቀረበለት? ከነበረ ታድያ ለምን ቀርቦ አልመሰከረም ለሚለውን ጥያቄ ተከሳሹ ያበጀለት መልስ ስለሌለ ተቀባይነት ያለው ሓሳብ አይደለም:: ሌላ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ ደግሞ ምንም እንኳ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ማለት እንዳመነ የማያስቆጥረው ቢሆንም የልዩ ዓ/ሕግ ምስክሮች ሲመሰክሩ ጊዜ የሰጡት ምስክርነት ለማስተባበል በ1ኛ ምስክር ላይ የቀረበ መስቀለኛ ጥያቄ ካለመኖሩ በላይ ሌሎች የቀረበም ቢሆን እንዴት አየችሁን ጨለማ አልነበረም ወይ ከማለት ውጭ ምስክሮቹ በአከባቢው አለ መኖራቸው ወይም በወቅቱ በጥበቃ ላይ እንደልተሰማሩ የሚጠቁም ጥያቄ አለማቅረባቸው የሚያመለክተው ነገር ቢኖር በመከ/ምስክሮቻቸው የተመሰከረ ከዓ/ሕግ ማስረጃ መስማት በኋላ የታሰበበት፣ የተመከረበትና ተጠንቶ የቀረበ መሆኑን ነው::

ባጠቃላይ የልዩ ዓ/ ሕግ ምስክሮች በተመሳሳይ ሁኔታ ያስረዱ ሲሆን ከምርመራ በኋላ ሚችን ማን ደግፎ አወጣው በሚለውን ላይ የተፈጠረ ልዩነትም ቢሆን ከአጠቃላይ የአመሳከከራቸው ሁኔታ ትልቅ ክብደት የሚሰጠው ልዩነት አይደለም:: ምክንያቱ በሌላ ነገር ብዙ የተንፀባረቀ ሁኔታ ስላልታየ ነው::

የተከሳሾች መከ/ምስክሮች ግን ምስክርነታቸው እርስ በራሱ የሚቃረን ከመሆኑም በላይ ተቃርኖውም በበርካታ ነገሮች የተንፀባረቀ ነው:: በአመሰካከራቸው ሂደት ብዙ ቀዳዳዎች የፈጠሩ ሲሆን ሆኖም ግን ቀዳዳዎቹ ሳይሸፍኑዋቸው የቀሩ ናቸው:: የልዩ ዓ/ሕግ ምስክሮች በወቅቱ ዞብ ላይ አልነበሩም ተከሳሾችም በግቢው አላደሩም በሚለው ነጥብ ብላ ብቻ ተንጠልጥለው ለመመስከር የሞከሩ ቢሆንም በጥናትና ተከሳሾችን ከተጠያቂነት እንዲ ያመልጡ ታቅዶ የተደረገ መሆኑ እንዳሰቡት ሳይሳካላቸው ቀርቷል:: ስለዚህ ተከሳሾች ከግብረአበሮቻቸው ጋር በመሆን በሚች አቶ ገ/ሄር ኪዳኑ ላይ በምርመራ ሂደት ደብደባ በመፈፀም ላይ ተሳታፊዎች በመሆን ለህልፈተ ሂወት የዳረጉዋቸው በመሆኑ በወ/መ/ሕግ ቁጥር 32/1/ሀ/ እና ሚችን የወያኔ ተባባሪ ነው በማለት የፈፀሙት ወንጀል በመሆኑ በወ/መ ሕግ ቁጥር 281/ ሀ/ መሰረት ጥፋተኞች ናቸው ስንል በሙሉ ድምፅ ውሳኔ ሰጥተናል::

የደርግ ወታደር የሚች ልብስ በደም ተጨማልቆ የወረወረላቸው መሆኑን ጠቅሰው ልጃቸው በካምፑ ውስጥ መገደሉን ሊያውቁ እንደቻሉ ነው::

ሌላ ያቀረበው ሰነድ ደግሞ በቁጥር 1422/ ጠ/702 ሰኔ 16/1968 ዓ/ም በተግሬ መሸኛ ደብዳቤ ተያይዞ የቀረበ 12 ገፅ ያለው ቃል ጉባኤ ሲሆን «ፀረ አብዮት» ሓይሎችና አባሎቻቸው ሊደመሰሱ እንዲሚገባ የተወሰነ ዕቅድና እንዲሁም ሕዳር 6/70 ዓ/ም በ32ኛ ዓመት በቁጥር 1467 የወጣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሆኖ ቀይ ሽብር መፋፋም እንዳለበት የተሰጠ መግለጫ ነው::

ፍ/ቤቱ ልዩ ዓ/ ሕግ የመሰረተው ክስና ያቀረበው ማስረጃ አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ መከላከል እንዳለበት በሰጠው ብይን መሰረት የሰውና የሰነድ ማስረጃ አቅርቦ አሰምቷል::

መከላከያ ምስክሮቹ ያስረዱልኛል ብሎ ያስያዘው ጭብጥ ተከሳሽ ግንቦት 5/1976 ዓ/ም ሚስቱ በምጥ ላይ ስለነበረች ከመከ/ምስክሮች ጋር አብሮ እቤቱ ማደሩን የደን ልማት ጠባቂ መኖሩን በወታደራዊ እንቅስቃሴ እንዳልነበረበት ሟች የደርግ ህዝባዊ ሰራዊት አባል እንደነበርና ኋላ ሸፍቶ በርሃ ስለገባ በደርግ ወታደሮች ተይዞ የተገደለ መሆኑን፣ በተጨማሪ ከ4ኛ 6ኛ ተራ ቁጥር ያሉ መከ/ምስክሮች ተከሳሽ 3 ወንድሞቹ ከተገደሉበት በኋላ ታሕሳስ መጨረሻ 1975 ዓ/ም ደርግ ትጥቁን ያስፈታው መሆኑንና ታስሮ መኖሩን፣ የልዩ ዓ/ሕግ ምስክሮች የሆኑት አቶ ሰንበታይ ሃይሉ እና ቤተሰቦቻቸው ከተከሳሽ ጋር በደን ጭፍጨፋ የተነሳ በ1977 እና 78 ዓ/ም ያስቀጣቸው በመሆኑ ፀብ እንደነበራቸው ነው:: በዚህ መሰረት መከ/ ምስክሮች የሰጡት ቃል አንድ በአንድ እናያለን::

1ኛ መከላከያ ምስክር አቶ ማቸ እምባየ የሰጡት ምስክርነት፣ ከመስከረም አጋማሽ 1976ዓ/ም ጀምሮ ከተከሳሽ ቤት የከብት እረኛ ሆኖው ይሰሩና ይኖሩ እንደነበር ገልፀው የተከሳሽ ልጆች እንደሚያውቋቸው በኩር ልጁ አበራሽ፣ ታናሽዋ አለሙ፣ ከዛ ጌታቸው ቀጥሉ ደግሞ መስፍን የሚባሉ መሆናቸው ምስክሩ እዛ ሳሉ የተወለደ ጌታቸው የሚባል መሆኑን የተወለደበት ጊዜ ደግሞ ጉንበት 5 ሆኖ ዓ/ምህረቱ ግን እንደሚያስታወሱት ተከሳሽ በወቅቱ ደኅል በሚባል ደን ጠባቂ እንደነበር፣ ደኑ ሲጠብቅ መሳርያ ያልነበረው መሆኑን፣ ንጉስ አባይን ወታደሮች ወስደው ገደሉት ሲባል እንደሰሙና ምክንያቱ ግን እንደማያውቁ ነው::

2ኛ መከላከያ ምስክር አቶ ብርሃኑ ሓዱሽ ሲያስረዱም፣ ከተከሳሽ አንድ መንደር ስለሆኑ እንደሚያውቁዋቸውና ተከሳሽ የታሰረውም ንጉስ አባይ ገድለሃል ተብሎ መሆኑን ተከሳሽ የደን ልማት ጠባቂ እንደነበርና በወቅቱ መሳርያ እንዳልነበረው ነው:: ተከሳሽ ልጆች አሉት በክር ልጁ አበራሽ፣ ቀጥሎ አለሙ፣

1144

የተከሳሽ ባለቤት ግን ሊኑጋ ሲል ደሮ ከጨኸ በኋላ ነበር የተገላገለችውን ከዛ እስኪኑጋ ድረስ እየወራን ቆየንና እኔ፣ካሕሳይ አረፋይኔ፣ ሃፍቱ አለሚ ሆነን ጥዋት ወደ ቤተክርስትያን ልንሳለም ሄድን በቤተክርስትያን ግቢ/ አከባቢ/ ደግሞ የንጉስ አባይ እናት ወ/ሮ ለምለም መንቆርዩስ የተባሉ ልጄ ወታደሮች ወሰዱብኝ ብላ ስታለቅስ አገኘናት፡፡ ከዛ ንጉስ አባይ ሙቷል ተባለና እናቱ ለቅሶ ተቀምጣ ስለነበር እኔ ከበላይ ገሰሰ እና ከንጉስ ወረታ ጋር ሄደን ደርሰናል፡፡ ንጉስ አባይ መጀመርያ ከደርግ ሚሊሻዎች ጋር ነበር ኋላ ግን ሸፍቶ በርሃ ላይ ነበር የሚቀመጠው ሲሉ አስረድቷል፡፡

በተጨማሪ ያስረዱት ደግሞ ተከሳሽ የደን ልማት ሲጠብቅ በነበረበት ጊዜ በደን ጭፍጨፋ ምክንያት ሰዎችን ያስቀጣ ስለነበር ከአከባቢው ህዝብ ግጭት ነበረው፡፡ ሁላችንም እንቀጣ ነበር፡፡ አቶ ሰንበታይ ሃይሉ ከዚህ ምክንያት የተነሳ ከተከሳሽ ጋር ቂም ነበራቸው፡፡ አቶ ሰንበታይ ሃይሉ ከሟች ንጉስ አባይ ጋር የአንድ አከባቢ ነዋሪዎች ከመሆናቸው በላይ የንጉስ አባይ ልጅ የክርስትና አባት ናቸው ብሏል፡፡

መከ/ ምስክሩ ስለራሳቸው ሁኔታ ተጠይቀው ልጆች አሉኝ የመጀመርያ ልጄ ልደት 29/1975 ዓ/ም ሲወለድ ታናሹ ልጄ ደግሞ ቀኑ በማላስታውሰው ጥር ወር እንደገባ በ1977 ዓ/ም ይመስለኛል የተወለደው፡፡ ያለፈው ዓመት ስንት ዓ/ምህረት እንደነበር አላውቅም በማለት መስክሯል፡፡

5ኛ መከ/ ምስክር አቶ ካሕሳይ አረፋይኔ የሰጡት ምስክርነት ስንመለከትም፣ ተከሳሽ የሚኖረው ሕጉም ብርዳ በተባለ አከባቢ ነው ስራውም የደን ልማት ጠባቂ ነበር ቀደም ሲል መሳርያ ይዞ ይጠብቅ ነበር ታሕሳስ 28/1975 ዓ/ም ግን ደርግ ወንድሞቹ ስለገደለበት አንስቶ እንደቀበራቸውና ከዛ ግን ለምን የተሓት ተባባሪዎች ቀበርክ በሚል ለ6 ወር ያህል እንዲታሰር አድርጓታል፡፡ ከዛ በኋላ ነው ትጥቁ እንዲፈታ ያደረገው፡፡ የተከሳሽ ልጆች አውቃቸዋለሁ፡፡ አበራሽ፣አለሙ፣ጌታቸው ንግስቲ መስፍን ዋሸኛ ይባላሉ ጌታቸው የተወለደው ጉንበት 5/1976 ዓ/ም ነው፡፡ይህ ላስታውሰው የቻልኹኝ ደግሞ ልጁ ሲወለድ እናቱ ምጥላይ ስለነበረች ብዙ ጭንቅ ስለነበረን ነው፡፡ ወደ ተከሳሽ ቤት የሄድኩት ከብቶቼን እንደስገባሁ ነው፡፡ የተከሳሽ ባለቤት የወለደችው ሌሊቱ ሊኑጋ ሲል ነበር፡፡ እኛ ደግሞ ፀሐይ እስክትወጣ ድረስ እዛው ቆየንና እኔ ፣ ሐጎስ ምስጉን እና ሃብቱ አለሚ ወደ ቤተክርስትያን ሄድን ፡፡ እዚያ እንደ ደረስን የንጉስ አባይ እናት ወ/ሮ ለምለም መንቆርዮስ ልጄን ጦር ወሰደብኝ ብለው ሲያለቅሱ አገኘናቸው፡፡ ከየት እንደወሰዱት ግን አላውቅም ንጉስ አባይ መጀመርያ የደርግ ታጣቂ ነበር፡፡ ከዛ በኋላ ግን ከድቶ በረሃ ሄዶ ስለነበር እንደገና ደርግ ይዞ በካምፕ ውስጥ ገደለው ይባላል፡፡ ያሉ ሲሆን በተጨማሪ ያስረዱት ደግሞ የተከሳሽ ባለቤት ጌታቸው ሲወልዱ ሌሊት ሐጎስ ምስጉን፣ ሃብቱ አለሚ፣

ከበደው ነጋሽ፣ ማቹ እምባዩ፣ ብርሃነ ሓዱስ እና ተከሳሽ ነበሩ። ከሴቶችም የባህል አዋላጅ የሆኑት ወ/ሮ ለምለም አየለ፣ እንዲሁም ወ/ሮ ለምለም አበራ፣ ታምራት አረጋዊ አበቡ ተ/መድህን ማናሹ ከበደም ነበሩ ብሏል።ሌላ የጠቀሱትም ተከሳሽ በወቅቱ ትጥቅ እንዳልነበረው፣ የደን ልማት ጠባቂ በነበረበት ጊዜ ደን ለሚጨፈጭፉ ያስቀጣቸው እንደነበር ከተቀጡት እሚያስታውሱዋቸው ደግሞ ምስክሩ ራሳቸው ፣ አቶ ስንበታይ ሃይሉ እና ብርሃነ ሓዱስ መሆናቸው ስንበታይ ሃይሉ ደን መጨፍጨፍ ስለማይተውና ተከሳሽም ማስቀጣቱ ስለማተው ከዚህ የተነሳ ፀብ የነበራቸው መሆኑን አውቃለሁ ብሏል።

በመጨረሻ ያሉት ደግሞ ያገባሁት ጥር 7/1971 ዓ/ም ነው 3 ልጆች አፍርቻለሁ። የመጀመርያ ልጅ ቀኑ በማላስታውሰው ሕዳር ወይ ይመስለኛል በ1974 ዓ/ም ነው የተወለደችው፡ ሁለተኛ ልጅ ግን መቼ እንደተወለደች አላስታውስም። ሶስተኛው ልጅ ጥር 23/ 1990 ዓ/ም ተወለደ በማለት አስረድቷል።

6ኛ መከላከያ ምስክር አቶ ሃብቱ አለሚ ሲያስረዱም ከተከሳሽ ጋር የምንኖርበት አከባቢ አንድ ስለሆነ እንተዋወቃለን ስራው የደን ልማት ጠባቂ ነበር።መጀመርያ ግብርና አስታጥቆት ቢኖርም ወንድሞቹ ከህወሓት ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ ደርግ በ28/4/75 ዓ/ም ስለገደላቸው ተከሳሽ ደግሞ ህዝቡን አስተባብሮ እንዲቀበሩ ስላደረገ ለምን ቀበርካቸው በሚል ምክንያት ከ3 ቀን በኋላ እንደታሰረና ትጥቁም እንዲፈታ የተደረገ መሆኑን አውቃለሁ ብሏል። አክለው የገለፁትም ተከሳሽ አበራሽ አለሙ፣ ጌታቸው፣ መስፍን፣ ንግስቲ፣ ዋሸኛ የሚባል ልጆች አሉት። ሌሎቹ የተወለዱበት ጊዜ ባላስታውስም ጌታቸው ግን ጉንቦት 5/1976 ዓ/ም ነው የተወለደው ይህንን ለማስታወስ የቻልኩኝ የተከሳሽ ባለቤት በምጥ ላይ ስለነበረች ጭንቅ ላይ ስለነበርን ብርሃነ ሓዱስ ጠርቶኝ ከብቶቼን እቤት ካስገባሁኝ በኋላ ህጂ በተከሳሹ ቤት ስላደርኩኝና በየዓመቱ ቀኑ ስለሚያስታውሱት ነው።በተከሳሽ ቤት ያገኘሁዋቸው ደግሞ ማቹ እምባዩ፣ ሓጎስ ምስጉን፣ ተከሳሽ ናቸው። የተከሳሽ ባለቤት የወለዱት ደግሞ ደሮ ደጋግሞ ከጨኸ ወደ ንጋት አከባቢ ነው ፀሃይ እስከ ትወጣ ግን እዛ ቆይተን ከካሕሳይ አረፋይኔ እና ሓጎስ ምስጉን ጋር ወደ ቤተክርስትያን ሄድን። ከቤተክርስትያኑ እንደደረስን ወ/ሮ ለምለም መንቆርዩስ አገኘናቸውና ምን ሆኖው ነው ብሎ ሓጎስ ምስጉን ሲጠይቃቸው ልጄን ንጉስ አባይ ሌሊቱ ወታደሮች መጥተው ከቤቱ አውጥተው ወሰዱት ብለው እያለቀሱ መለሱልን። ንጉስ አባይ መጀመርያ የደርግ ታጣቂ ነበር ኋላ ግን ሸፍቶ ስለነበር ህዝብም ንብረታችን እየዘረፈን ነው ብሎ ለመንግስት ያመልክት ነበር በማለት አስረድቷል። መከ/ ምስክሩ ከዚህ በተጨማሪ የሰጡት ቃል ቢኖር ተከሳሽ የደን ልማት ጠባቂ በነበረበት ወቅት ደን የሚጨፈጭፉ

1148

የተወለዱበትን ጊዜ በትክክል ለማወቅ ያልቻሉ ናቸው 2ኛ መከላከያ ምስክር ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት መሆኑን ጠቅሶ በ1981 ዓ/ም እንዳገባ በ1986 እና በ1989 ዓ/ም የመጀመርያና ሁለተኛ ልጆቹን እንደወለደ ነገር ግን ያገባበትንና ልጆቹ የተወለዱበትን ቀንና ወር እንደማያውቅ አስረድቷል 3ኛ መከ/ ምስክር በበኩላቸው ባለ ትዳርና የልጅ እናት መሆናቸውን ጠቅሰው መቼ እንዳገቡ ልጃቸውን መቼ እንደወለዱ ከዚያም አልፎ ያለፈውንና ያሁኑን ዓ/ምህረት እንኳን ሊያውቁ እንደማይችሉ አስረድተዋል:: 4ኛ መከ/ምስክር ደግሞ የመጀመርያ ልጁን ጥር 24/75 ዓ/ም ሁለተኛ ልጁን ቀኑን በማያውቅበት ጥር/ 77ዓ/ም እንደተወለደ ቢጠቅስም ምስክርነቱ ግምታዊ ስለነበር ጥር ማለት ስንተኛ ወር ነው ሲባል አላውቅም ብሏል:: 5ኛ መከላከያ በበኩሉ ጥር 7/71 እንዳገባ ጠቅሶ ሁለተኛ ልጁ የተወለደበትን ቀን፣ወርና ዓ/ምህረት ማወቅ እንደማይችል በሰጠው ምስክርነት አረጋግጧል፡ 6ኛ መከላከያ ደግሞ በ1973 እንዳገባ የመጀመርያ ልጁን ነሓሴ 78 ዓ/ም ሁለተኛ ልጁን የካቲት /80 ዓ/ም እንደተወለደ ቀኑ ግን እንደማያስታውስ ከገለፀ በኋላ በፍ/ቤቱ ማጣርያ ጥያቄ የመጨረሻ ልጁን ዕድሜና መቼ እንደተወለደ ተጠይቆ ዕድሜው 6 ዓመት ሆኖ የተወለደበት በ1989 ነበር በማለት መላምታዊ ቃል ሰጥቷል::አንድ ምስክር ይህን አውቃለሁ ስላለ ብቻ የተናገረው ሁሉ እውነት ነው ሊባል አይችልም::የምስክር ቃል መመዘን የሚኖርበት ከተጨባጩ ሁኔታ በመነሳትና አጠቃላይ ጉዳዩን በመገመት መሆን ይኖርበታል፣ የመከላከያ ምስክሮቹ የራሳቸው ልጆች የተወለዱበትንና ራሳቸው ጋብቻ ያደረጉበትን ከዚያም ሲያልፍ አሁን ያሉበትን ዓ/ምህረት ሳያውቁ የሌላውን ለማወቅ ይችላሉ ማለት በጣም ይከብዳል፣ የተከሳሹ ልጅ/ ጌታቸው/ ግንቦት 5/76 መወለዱን አሁን እንዴት አስታወሳችሁ ሲባሉ የሰጡት ቃል ልደቱን በየዓመቱ ስለሚያከብሩለት የሚል ሰንካላ መልስ ሰጥተዋል:: ይህን በዚህ መልኩ ካስታወሱ የነሱስ ልጆች ልደታቸው አይከበርም? የተከሳሹ ሌሎች ልጆች በተለይ በግንቦት 5/76 ዓ/ም ከተወለደው ልጅ በኋላ የተወለዱትስ ልደት አይደረግላቸውም? ባጠቃላይ ሲታይ መከላከያ ምስክሮቹ ተከሳሽ ተከላከል የተባለበት ጉዳይ የተፈፀመበት ቀን ለማጥናት ብቻ የሰጡት መከ/ ምስክርነት እንጂ የእውነት እንዳልሆነ መገመት ይቻላል:: ሌላው የመከ/ ምስክሮቹ በተጨማሪ የሰጡት ቃል ተከሳሽ ደን ጠባቂ ሆኖ መሳርያ እንደማይዝ ደን በመቁረጥ የተነሳ የልዩ ዓ/ ሕግ 29ኛ ምስክርን በማስቀጣቱ ቂም እንዳላቸው ሲሆን መከላከያ ምስክሮቹ በጥናት የቀረቡ ስለሆኑ በዚህ ዙርያም እውነተኛ ምስክርነት ይሰጣሉ ተብሎ አይታሰብም::

በደን መቁረጥ ምክንያት ተከሳሽ ከ28ኛ የልዩ ዓ/ ሕግ ምስክር አቶ ሰንበታ ሃይሉ ጋር ቅሬኔ አላቸው በማለት ከ4-6 የተጠቀሱት ምስክሮች የመሰከሩ ቢሆንም

1150

ምስክርነታቸው እርስ በራሱ የተቃረነ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይሆንም:: 4ኛ መከ/ምስክር ተከሳሽ ያስቀጣው 1/ 28ኛ የልዩ ዓ/ሕግ ምስክር 2/ እሱ ራሱን ብቻ እንደ ሆነ የመሰከረውን 5ኛመ/ ምስክር ደግሞ 28ኛ የልዩ ዓ/ሕግ ምስክርን ብርሃኑ ሃዲስ/ 2ኛ መከ/ምስክር/ እና እሱ ራሱን ብቻ እንዳስቀጣ በመመስከር ሲቃረን 6ኛ መከላከያ በበኩሉ በተከሳሽ የተቀጡት 28ኛ የልዩ ዓ/ሕግ ምስክርና የብርሃኑ አዲስ አባት ብቻ ናቸው ከእነዚህ ውስጥ የተቀጣ አልነበረም በማለት በተለየ አቅጣጫ ተቃርኗቸዋል::

ተከሳሽ የሰው ማስረጃ እንዳበቃ ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ ሲሆን ሰስቱም ደብዳቤዎች የተፃፉት ተከሳሹ ተከላከል የተባለበት የወንጀል ድርጊት ከተፈፀመ በኋላ/ ከግንቦት 5/76/ በመሆኑ ይህንን ክስ ለማስተባበል በሚያስችል አግባብነትም ሆነ ብቃቱ ያላቸው አይደለም:: በክሳችን ተከሳሽ ታጣቂ ነበር የሚል እንጂ ፖለቲካዊ ወይም መንግስታዊ ስልጣን ነበረው በሚል ነገር አልተጠቀሰም:: ታጣቂ መሆን ደግሞ ከማናቸውም መንግስታዊ ግላዊ ስራ በተደራቢነት የሚገኝ እንጂ ፖለቲካዊ ወይም መንግስታዊ ሹመት የሚያስፈልገው አይደለም::

የልዩ ዓ/ ሕግ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃ ተከሳሽ 15ኛ ተከሳሽ ከነበረው ግብረ አበሩ ጋር ሆኖ ንጉሰ አባይን በሌሊት ይዘውት እንደሄዱ እና በሕጉም ብርዳ ካምፕ እንዲታሰር ተደርጎ ከዛ የደረሰበት እንዳይታወቅ ለማድረጉ ሲያስረዱ፣ የተከሳሽ መከላከያ ምስክሮች ግን በጥናት ተመስርተው የቀረቡ ከመሆናቸውም በላይ ስለንጉሰ አባይ በወታደሮች ተይዞ ተገደለ ሲባል ሰማን ከማለት በስተቀር እንዴትና በማን እንደተያዘ የሚያውቁ አይደለም:: እነዚህ መከላከያ ምስክሮች ንጉሰ አባይ ከደርግ የታጠቀውን መሳርያ ይዞ ሸፍቶ ነበር ወደ ቤቱም አይመጣም ካሉ በኋላ ግንቦት 5/76 ዓ/ም ከተከሳሽ ቤት አድረን ወደ ቤተክርስትያን ስንሄድ እናቱ ልጄን ወታደሮች ወሰዱብኝ እያሉ ሲያለቅሱ አይተናል በማለት 4ኛ 5ኛ እና 6ኛ መከ/ ምስክሮች የሰጡት ቃል በራሱ ሃሰተኛ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው:: ንጉሰ አባይ ከደረግ የታጠቀውን መሳርያ ይዞ ሸፍቶ ነበር ከአከባቢም አይመጣም ነበር ከተባለ ወላጅ እናቱ ከቤት ሆኖው በረሃ ያለው ልጃቸው የሚያዝበትን ሁኔታ የሚያውቁበት ዕድሉ እንዴት ሊኖራቸው ይችላል? ይህ የሚያሳየን የተከሳሹን የወንጀል ጥፋት ወደ ማይታወቁ ወታደሮች በመላክ ተከሳሹን ነፃ ለማውጣት በሚያስችል መልኩ ጥናታዊ ምስክርነት መስጠታቸውን ነው::

ስለዚህ የቀረቡት የመከላከያ ምስክሮች በጥናትና ተመስርተው የቀረቡና የመሰከሩ ቢሆንም ምስክርነታቸው የተምታታና ተአማኒነት የጎደለው በመሆኑ የሰነድ ማስረጃዎቹም ተከሳሽ ተከላከል የተባለበትን ክስ ለማስተባበል አልቻሉም::በመሆኑም

ልጄን ወሰዱብኝ ሊሉ የቻሉ? 6ኛ መከላከያ ምስክርስ በበርሀ ሽፍቶ ነበር እያሉ ከቤቱ እንደተወሰደ እናቱን ነገሩን ማለታቸው ምስክርነታቸው እርስ በራሱ አይጋጭም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች የሚያስነሱና መልስ ግን ያልተበጀላቸው ናቸው።

የልዩ ዓ/ ሕግ ምስክሮች አንድ ቤተሰብ ናቸው በተለይ 28ኛ ምስክር ለአቶ ሰንበታይ ሃይሉ በደን ጭፍጨፋ ምክንያት ተከሳሽ የደን ጠባቂ ሳለ በተደጋጋሚ ያስቀጣቸው ስለነበር ቂም አላቸው የሚል በመከላከያ ምስክሮች ቢገልፅም የልዩ ዓ/ ሕግ ምስክሮች ሲመሰክሩ ጊዜ ግን ይህ ዓይነት ተቃውሞ በተከሳሽ አልቀረበም ብቻ ሳይሆን በመስቀለኛ ጥያቄም ቢሆን አልተነሳም።የእውነት ቢሆን ኖሮ ፍ/ ቤቱ ግንዛቤ እንዲወስድለት ብሎ ባነሳው ነበር። ምስክሩም ከተከሳሽ ጋር ፀብ ያላቸው መሆኑን አለመሆኑን በፍ/ቤቱ ተጠይቀው የለንም ብለው ነው በተከሳሽ ፊት ያስመዘገቡ። ስለዚህ ከተመሰከረበት በኋላ ለመከላከል ተብሎ የቀረበ የፈጠራ ሐሳብ መሆኑን ነው የሚያስገነዝበን።

ተከሳሽ በወቅቱ የደን ልማት ጠባቂ ነበር ይህን ዓይነት ድርጊት ለመፈፀም ስልጣን አልነበረውም ለተባለውም የክሱ አቀራረብም ታጣቂ ሆኖ ድርጊቱ ፈፀመ የሚል እንጂ ይህ ዓይነት ስልጣን ነበረው አልተባለም። የደን ልማት ሰራተኛ ሆኖ ይህ ዓይነት ድርጊት እንዳይፈፅም የሚከለክለው የለም። በወቅቱ የተለያዩ የመንግስት ስራ የነበራቸው በእንደዚህ ዓይነት ድርጊት መሳተፍ የተለመደ እንደነበር የሚታወቅ ነውና። የሰነድ ማስረጃዎቹም ከዚህ አንፃር ሲታይ ጠቀመይታ ያላቸው አይደሉም። ከ1975 ዓ/ም በፊት ካልሆነ በስተቀር ከዛ በኋላ ትጥቁን ፈትቷል የተባለውንም ተከሳሹን ነፃ ለማውጣት የታለመ እንጂ ከሌሎች የአመሰካከር ሁኔታዎች ተገናዝቦ ሲታይ ተአማኒነት ያለው አይሆንም።

በአጠቃላይ የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የልዩ ዓ/ሕግ ማስረጃ ማስተባበል ያልቻለ፣ መከላከያ ምስክሮቹ የሰጡት ምስክርነት የራሳቸው ጉዳይ ሳያውቁ የሌላ ሰው እንደሚያውቁ ሆኖው በመቅረብ ከማስታወስ ችሎታቸው በላይ በመሄድ ለመመስከር የሞከሩ እንጂ እውነታ ያለው ምስክርነት ሰጥተዋል ሊባሉ አይቻልም. ስለዚህ ተከሳሽ የልዩ ዓ/ ሕግ ማስረጃ በመከላከያ ማስተባበል ስላልቻለ ተከለከል በተባለበት በወ/መ/ሕግ ቁጥር 32/1/ለ 281/ሐ/ መሰረት የወ/መ/ሕ/ስ/ስ ቁጥር149/1/ በሚያዘው በሙሉ ድምፅ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥተናል።

ዳኛ/ ገብሩ/ ፡ ቀጥለን ቅጣት በተመለከተ ሃሳብ እንቀበላለን መጀመርያ ልዩ ዓ/ህግ

ልዩ ዓ/ ህግ፡ እሺ ክቡር ፍርድ ቤት ዛሬ ጥፋተኛ በተባሉት ሦስት ተከሳሾች ላይ ያለኝን የቅጣት ሃሳብ አቀርባለሁ። 16ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ጥፋተኛ የተባለው ባንድ ድርጊት ነው ጥፋቱንም በፈፀመ ጊዜ ተራ የደን ልማት ሰ

መሰረት በሚሰጠው ቃል ለዛሬው በምናስይዘው ጭብጥ ቃላቸው እንዲሰጡና በዛ እንጨርሳለን የሚል ግምት ነው ያለን

ዳኛ/ ገብሩ/ የቀረው ባይቀርብም በቃ እንደለ ይቀራል ማለት ነው? ማለት አያስፈልጋችሁም ማለት ነው ?

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ: አዎ እንደዛ ነው::

ዳኛ/ ገብሩ/: እሺ 17ኛ ተከሳሽስ?

የ17ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ ሰለሞን ሃብቴ: ያው የኛም አራት መከላከያ ምስክሮች ነበሩን ወደ ችሎቱ አደራሽ እስከምንገባ ድረስ ሁለቱም ብቻ ነው ያየናቸው ሁለቱም አልመጡም ነበር እንግዲህ ሁለቱን አሰምተን ሁለቱ ደግሞ ለመጥራት ነው ሃሳባችን ከፈቀደልን ክቡር ፍርድ ቤቱ ምክንያቱም አንደኛው እዚህ ማረሚያ ቤት ስለሆነ ምንም ችግር የለውም አንደኛው ግን ከቀሩት ጋር ሆኖ ወረዳው የሚኖሩበት አከባቢ የተለያዩ ስለሆነ ምናልባት በዚሁ ተሰምቶ የሚሄድ ከሆነ::

ዳኛ/ ታደሰ/: ከ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ የተረዳነው ጠቅላላ ለዛሬ ሊቀርቡ የታሰቡ ምስክሮች ሦስት ሆነው ሁለቱ እንደቀረቡ እና አንደኛው ከደረሰ ይደርሳል ካልደረሰ ግን ሁለቱ የቀረቡ ምስክሮች ለዛሬው እንዲያስሙ ነው የተረዳነው::

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ አዎ ነገሩ ግን በዛሬ በምናስይዘው ጭብጥ ብቻ ነው ለዛሬ የሚቀርቡ ምስክሮች ሌሎቹ በሌላ ጭብጥ ስለሆነ በሌላ ቀን ቀጠሮ እናቀርባለን

ዳኛ/ ታደሰ/: ሌላው ተከሳሽ በ142 መሰረት ቃሉ ይሰማል ነው የተባለው?

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ አዎ

ዳኛ/ ታደሰ/: እሺ ይስጥና ወደ ምስክሮች እንገባለን

3ኛ ተከሳሽ ገ/ስላሴ ካሳ: ክቡር ፍርድ ቤት እኔ የተከሰስኩበት የህዝብ ድርጅት ካድሬ በመሆን በአድዋ አውራጃ በፈፀመው ወንጀል የሚል ነው:: እኔ ግን የህዝብ ድርጅት ካድሬ አልነበርኩም የቀይ ሽብር ኮሚቴም አባል አልነበርኩም እኔ የግብርና ሚኒስቴር ሰራተኛ ነኝ የነበርኩ በ1971 ዓ/ም በግብርና ሚኒስቴር ተቀጥሬ ከ1971 - 1974ዓ/ም በእንደርታ አውራጃ በሕንጣሎ ወረዳ የግብርና የልማትና ማህበራት ሰራተኛ ነኝ የነበርኩት ስለዚህ በዛን ጊዜ የማሰር የመመርመርና የማዘዝ ሃላፊነት ወይም ስልጣን አልነበረኝም ስለዚህ እንድያውም ለራሴን በዛን ጊዜ የሕ.ወ.ሓ.ት አባል እየተባልኩ ስታሰርና ስፈታ የነበርኩበት ጊዜ ነው እና የምሰጠው ቃሌ ይህ ነው አመሰግናለሁ::

ዳኛ/ ታደሰ/: እሺ በዛሬው ቀን የቀረቡ ምስክሮች የሚመሰከሩበት ጭብጥ ይመዝገብ::

1157

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ: ጭብጡ ተከሳሽ ከ1971-1974 ዓ/ም በሕንጣሎ ወረዳ የግብርና ሚኒስቴር ሰራተኛ እንደነበሩ እና በወቅቱ የህዝብ ድርጅት ካድሬ እንዳልነበሩ የሚመስክሩ ናቸው እና ምስክሩ 1ኛ አቶ ሃይሉ መሓሪ ይባላሉ::

ዳኛ/ ታደሰ/: እሺ ምስክር ይጠሩ

→ ምስክሩ በእውነት የሚመሰክሩ መሆናቸን ቃለ መሓላ ከፈፀሙ በኋላ እንደሚከተለው መስክሯል::

ዳኛ/ ታደሰ/: ስምዎ?

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ ምስክር: ሃይሉ መሓሪ ሃይሉ

ዳኛ/ ታደሰ/: እድሜ?

1ኛ መ/ ምስክር: አምሳ/50/

ዳኛ/ ታደሰ/: ስራ?

1ኛ መ/ ምስክር: ግብርና

ዳኛ/ ታደሰ/: አድራሻ?

1ኛ መ/ምስክር: ሳምረ / ሳሕርቲ ሳምረ ወረዳ/ ቀበሌ ሳምረ

ዳኛ/ ታደሰ/: የመጡበት ምክንያት ያውቃሉ ?

1ኛ መ/ ምስክር አዎ

ዳኛ/ ታደሰ/: በምን ምክንያት ነው?

1ኛመ/ ምስክር መጥርያ ስለደረሰኝ

ዳኛ/ታደሰ/: የምን?

1ኛመ/ምስክር: የምስክርነት

ዳኛ/ታደሰ/: በማን?

1ኛመ/ምስክር: በአቶ ገ/ስላሴ ካሳ

ዳኛ/ ታደሰ/: ትተዋወቁ አላችሁ?

1ኛ መ/መስክር አዎ እንተዋወቃለን

ዳኛ/ ታደሰ/: ከመቼ ነው የምትተዋወቁት?

1ኛ መ/ ምስክር: ያው አብረን እንሰራ ነበርን ግብርና

ዳኛ/ ታደሰ/: ዝምድና አላችሁ?

1ኛ መ/ ምስክር: የለንም

ዳኛ/ ታደሰ/: እሺ ዋና ጥያቄ ይቅረብ

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ አቶ ሃይሉ መሓሪ ያው ለፍርድ ቤቱ እንደገለፁት ከተከሳሽ

1158 እንደምትተዋወቁና በግብርና አብራችሁ ስትሰሩ እንደነበራችሁ ገልፆዋል በለዚህ ትውውቃችሁ ከመቼ እስከ መቼ እንደነበር ይግለፁልን::

[redacted]

1100

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ምስክር 74 ታህሳስ ላይ እስከታህሳስ ወር74 ዓ/ም ነበርኩኝ እዛ፣ እሱ ከዚያ በኋላ ነው የተዛወረው እና ወሩ አመተ ምህረቱ ግን ብዙ ጊዜ ስለሆነ ምናልባት ቀኑ በትክክል ለማወቅ የሚቻል አይመስለኝም ማለት የወሩ ካልሆነ በስተቀር

ልዩ ዓ/ህግ አይደለም እኔ የምጠይቅዎት ከ71 73 ብለው ነበር አሁን ደግሞ 74 ብለው ነበር የትኛው ነው ትክክል አብራችሁ የቆያችሁት?

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ምስክር እኔ እስከ 73 ዓ/ም እዚያ እንደነበረ እና 74 ዓመተ ምህረትም እኔ እዛ ነበርኩኝ ግን ዝውውር የመጣለት ትዝ የሚለኝ ወደ 74 መጨረሻ ሳይሆን አይቀርም 74 አጋማሽ ወር እኔ ግን እዚያ ነው የነበርኩት

ልዩ ዓ/ህግ ስለዚህ እርስዎ ከርስዎ ጋር መቼ ነው ዝውውር አግኝቶ የሄደው ወይም ከርስዎ መስርያ ቤት ለቆ ወደ ሌላ የሄደው መቼ ነው?

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ ምስክር ወደ ግብርና የሄደው ታህሳስ እንግዲህ ግብርና ጠራው 74 ዓ/ም ጥር ወር ላይ ግብርና ጠርቶታል እና ጠርቶ የመደበው የት ቦታ እንደሆነ አላውቅም እና እዚያ ወረዳ አብረን እንደነበርን እኔ ግን እዚያ ትቶኝ እንደሄደ ማለት እዚያ ግብርና ስሰራ ነው የነበርኩት እኔ

ልዩ ዓ/ህግ እርስዎስ መቼ ተዛወሩ?

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ምስክር፡ እኔ እንግዲህ ወደ እሱ ከሄደ በኋላ ቆይቼ አለሁ እዚያ ቆይቼ አለሁ

ልዩ ዓ/ህግ መቼ ተዛወሩ ነው ጥያቄው?

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ መስክር ወደ 74 ዓ/ም ከሱ በኋላ ነው የተዛውርኩት እሱ ከሄደ በኋላ

ልዩ ዓ/ህግ አዎ አይ በኋላ በሚለው ሳይሆን በጊዜ እስቲ ይጥቀሱልን

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ምስክር እንግዲህ ከዛ ተነስቼ ወደዚህ ነው የመጣሁት

ልዩ ዓ/ህግ ይቅርታ እኔ የምፈልገው በጊዜ ነው በዚህ ጊዜ እሱ ሄደ በዚህ ጊዜ እኔ እንደዚህ ሆንኩ እያሉ እስቲ ለፍ/ቤቱ ይግለፁ

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ምስክር እኔ በጊዜው ምን መሰልዎት እንግዲህ በትክክል እስከ 74 ዓ/ም አብረን ነበርን እንግዲህ ታህሳስ ወር ወደ ክልል ተዛውሮ ሄደ እሱ እኔ እዚያው ወረዳ ውስጥ ነበርኩኝ

ልዩ ዓ/ ህግ፡ ዝውውር ከግብርና የመጣለት ጥር 74 ዓሉ ከዛ ታህሳስ 74 ተዘዋወረ ማለት ነው እንዴት ነው እዚህ ላይ?

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ ምስክር አይደለም ታህሳስ መጣለት ወደ ጥር ከጥሩ አንድ ነው የተዛወረው

1160

ዳኛ/ ታደሰ/: እርስዎና ወ/ሮ ባፌና በሕንጻሉ ወረዳ ማን ነው መጀመርያ እዝያ ቦታ የተመደበው?

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ ምስክር ከኔና ከወ/ሮ ባፌና እኔ ነኝ

ዳኛ/ ታደሰ/ : ወ/ሮ ባፌናስ ከመቼ አመተ ምህረት ጀምረው ነው እዛ ስራ ላይ የተመደቡት?

የ3ኛ ተከሳሽ 1ኛ መ/ምስክር ከአቶ ገ/ስላሴ ከሱ በፊት ነው የተመደበችው አልሞስት 70 ዓ/ም ይሁን ኢኒሂው ከኛ በኋላ ባች ነች የመጀመርያ የገጠር ልማት ወኪል ማለት የኑሮ ዘዴ ነው የሚባለው በዝያን ጊዜ እስዋንም በዝያ ጊዜ በወረዳው ለመጀመርያ ጊዜ የተመደበችው በኑሮ ዘዴ እስዋ ነች፡፡

ዳኛ/ ታደሰ/: እሺ ጨርሰዋል ይነሱ ቀጣዩ ምስክር ይጠሩ

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ጠበቃ 2ኛ መ/ ምስክራችን ወ/ሮ ባፌና ወልዱ ይባላሉ

→ ምስክርዋ በእውነት የሚመሰክሩ መሆናቸውን ቃለ መሓላ ከፈፀሙ በኋላ እንደሚከተለው መስክሮዋል፡፡

ዳኛ/ ታደሰ/: ስምዎ?

የ3ኛ ተከሳሽ 2ኛ መ/ ምስክር: ወ/ሮ ባፌና ወልዱ ገብሩ

ዳኛ/ ታደሰ/: እድሜ?

የ3ኛ ተከሳሽ 2ኛ መ/ምስክር:አርባ ሦስት

ዳኛ/ ታደሰ: ስራ ?

2ኛ መ/ ምስክር ግብርና ሚኒስቴር

ዳኛ/ ታደሰ/: አድራሻ?

2ኛ መ/ምስክር እንደርታ ወረዳ ከተማ ኹሓ ቀበሌ 06

ዳኛ/ ታደሰ/ በምን ምክንያት ነው የመጡት?

2ኛ መ/ ምስክር: በቢሮየ በፅሁፍ እንደተነገረኝ ለምስክርነት ተጠርተሻል ተብየ ነው የመጣሁት

ዳኛ/ ታደሰ/: በማን ነው ?

2ኛ መ/ምስክር በአቶ ገ/ስላሴ ካሳ

ዳኛ/ ታደሰ/: ትተዋወቁ አላችሁ?

2ኛ መ/ምስክር: አዎ በግብርና ሚኒስቴር

ዳኛ/ ታደሰ/: ዝምድና አላችሁ?

2ኛ መ/ ምስክር: የለንም

ዳኛ/ ታደሰ/: ለአቶ ገ/ስላሴን አሁን ማወቅ ይችላሉ ?

2ኛ መ/ ምስክር: አዎ እችላለሁ

1164

[redacted]

ዳኛ/ ታደሰ/ እሺ ዋና ጥያቄ ይቅረብ

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ ወ/ሮ ባፊና ወልዱ ከተከሳሽ ጋር በግብርና ሚኒስቴር እንደምትተዋወቁ ገልፀዋል የግብርና ሚኒስቴር የት የነበረ ሚኒስቴር ነውና መቼ አመተ ምህረት እንደነበረ ይግለፁልን

2ኛ መ/ ምስክር: ከአቶ ገ/ስላሴ ከሳ ጋር የምንተዋወቀው በ1971 ዓ/ም እኔ ከት/ቤት ባኮ ከሚባለው የግብርና ማሰልጠኛ ወጥቼ ለስራ ሙከራ ተብሎ ዓዲጉዶም ወረዳ ነበር የተመደብነው ያኔ ዓዲጉዶም ነበር የሚባለው ሕንጣሎው ለብቻው ስለነበር የተመደብኩት በዚህ በኑሮ ዘዴ ነው ሴቶችን ነው የማስተምረው ባልትናን አቶ ገ/ስላሴ ደግሞ ያኔ ተከታትለው መጡ ማህበራት ማደራጃ ተብለው እና እዛ ነው የምንተዋወቀው ያው የትውውቃችን ጊዜ በ71 ዓ/ም ማለት ነው እዛ ወረዳ ውስጥ

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ጠበቃ: ከ1971 እስከ ስንት አመተ ምህረት ነበር አብራችሁ የነበራችሁ ወይም የምትተዋወቁት?

2ኛመ/ምስክር: 72 ዓ/ም እኔ ክልል ገባሁ ንብረት ክፍል ተብየ ያው እዛ ክልል ሲመጡ ነው እማያቸው ከ73 ጀምሮ ግን መዋቅር መጣ እኔ ዓዕዳ እምባ ወረዳ ተመደብኩኝ ከዛ በኋላ አልተገናኘንም እና አሁን የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ እኔም እዚህ ስመጣ ግብርና ሚኒስቴር መልሼ ነው ያገኘሁዋቸው

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ጠበቃ የት ነው?

2ኛ መ/ምስክር: እዚህ ክልል ግብርና

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ: እርስዎ በ72 ክልል እንደተመደቡና በ73 ዓዕዳ እምባ እንደተመደቡ ነው የገለፁት እርስዎ በወቅቱ በዚሁ አመተ ምህረት በጠቀሱት 72 -73 ዓ/ም ተከሳሽ የት ነው የነበሩት ማለት ትክክለኛ ስራቸውም?

2ኛ መ/ምስክር: ሰባ ሁለት ያው ክልል ነበርኩ ወደ ግብርና ሲመጡ ነው እማያቸው ለክብር ለስብሰባ ምናምን ሲጠሩ ያው ወረዳ ሰራተኛው ወደ ክልል ይመጣል እዛ አያቸው ነበር በ73 ግን መዋቅር ስለነበር እኔም ራሴ ከእንደርታ አውራጃ ከሚባለው ለቅቄ ወደ ሁለት አውላዕሎ አውራጃ ወደ ዓዕዳ እምባ ነው የሄድኩት ከዛ በኋላ ነው የተቋረጠው ማለት ነው ግንኙነታችን

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ጠበቃ እሳቸውስ የት ሄዱ?

2ኛ መ/ምስክር: መዋቅሩ የት እንደመደባቸው እኔ ያኔ እንትን አላልኩም

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ ከወረዳ ነበር ወደ ክልል ለስብሰባ የሚመጡት ብሎዋል ከየትኛው ወረዳ ነበር የሚመጡት?

2ኛ መ/ምስክር ከተዘወርን በኋላማ በ85 እዚህ ስንመጣ ነው ያገኘሁት

ልዩ ዓ/ህግ፡ እሺ ጨርሼ አለሁ

ዳኛ/ ታደሰ/ ድጋሚ ጥያቄ ካለ? የለም

## የፍርድ ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ

ዳኛ ታደሰ/፡ ዓዲጉዶም ያሉት ቀድም ሕንጣሎ ዓዲጉዶም እያሉ ይጠሩት የነበረው ቦታ መቼ ነው የተመደቡት?

2ኛ መ/ምስክር እኔማ ያው 70 ሃምሌ ነው ወደዛ የገባሁት ከዛ ግን ከዛ ለቅቄ የወጣሁት መስከረም ውስጥ 72 ነው ወደ ክልል ንብረት ክፍል ሁኘ እንድሰራላቸው የተመደብኩት

ዳኛ/ ታደሰ/ እዚያ 70 ሃምሌ የተመደቡት ከሆነ ተመድበው ሲሄዱ ተከሳሽ እዚያ ነው ያገኙት ወይስ ከርስዎ በኋላ ነው የመጣው?

2ኛ መ/ ምስክር፡ እኔ ሃምሌ ሄድኩኝ እሱ ግን መስከረም ይሁን ጥቅምት እንደዚህ ነው የመጣው በተወሰኑ ወራት ልዩነት አለን

ዳኛ/ ታደሰ/ መስከረም ይሁን ጥቅምት አመተ ምህረቱ መቼ ነው?

2ኛ መ/ ምስክር፡ ሰባ አንድ አመተ ምህረት

ዳኛ/ ታደሰ/፡ ከ71 ዓ/ም እስከ 72 መስከረም አብራችሁ ለሁለት አመት አብራችሁ ነበራችሁ ማለት ነው?

2ኛ መ/ምስክር፡ አብረን አንድ ላይ እዛ ቢሮ እንሰራ ነበርን እኔ በኑሮ ዘዴ እሱ ማህበራት ማደራጃ

ዳኛ/ ታደሰ/፡ በዚያን ጊዜ የግብርናው አስተባባሪ ወይም ሃላፊ የነበረው ማን ነበር?

2ኛ መ/ምስክር፡ የኢፒድ ደስታ ኪዳነ ይባል ነበር፣ የእርሻና ህዝብ ማስፈር ደግሞ ክፍሉ ወልደኪሮስ

ዳኛ/ ታደሰ/ በዚያን ጊዜ ሕንጣሎና ዓዲጉዶም እንዴት ነው ልዩነት ነበረው ወይስ አንድ ወረዳ ነው

2ኛ መ/ምስክር፡ አዎ ነገሩ ሁለት ወረዳ ነው በእርሻና ህዝብ ማስፈር አንድ ወረዳ ነው መሬት ይዞታ ማለት ነው በኢፒድ ግን የሆነ ፕሮጀክት ስለነበረ እኛ ዓዲጉዶም ነበር ቢሮአችን ግን ሁሉም ወረዳ እናጠቃልለው ነበር እስከ ደንጎላት ድረስ እስከ ማርያም ደብረሓይላ ምችአል ደብረሓይላ እስከ መልሸዓቸብ ጠሊ የሚባለው ነበር የምናጠቃልለው።

ዳኛ/ ታደሰ/፡ ኢፒድ የምትሰሩ የነበራችሁ እርስዎ ኢፒድ ነበሩ ወይስ እንዴት ነው ?

2ኛ መ/ምስክር፡ ኢፒድ ነበርኩ እኔ

ዳኛ /ታደሰ/ ተከሳሹስ ?

1167

2ኛ መ/ ምስክር፡ ኢፒድ ነው እሱም

ዳኛ/ታደሰ/፡ ስለዚህ ቢሮአቸሁ የት ነበር ማለት ነው ?

2ኛ መ/ምስክር እኛ ዓዲጉዶም ነበርን ለአርሸና ህዝብ ማስፈር ለአቶ ክፍሉ ስንፈልግም ሕንማሎ ነበር የምንሄደው

ዳኛ/ ታደሰ/፡ ስለዚህ ዋና መኖሪያችሁ የት ነበር እናንተ ሕንማሎ ነው ወይስ የት ነው?

2ኛ መ/ምስክር፡ ዓዲጉዶም ነበር

ዳኛ/ ታደሰ/፡ በዝያን ጊዜ አቶ ሃይሉ መሓሪ ምን ይሰሩ ነበር?

2ኛ መ/ምስክር፡ የልማት ሰራተኛ ነበሩ ዓዲጉዶም ያው ዓዲጉዶም ሆነን እስከ መልበ ዓቐብ ጠሲ ነበር ሁሉ ወረዳ እና ጠቃልለው ነበርን፡፡

ዳኛ/ ታደሰ/፡ እሺ ምስክርነት ጨርሽዋል እና ይነሱ

የ3ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ፡ በቃ በዚሁ እናበቃለን ለዛሬው ማለት በዚሁ ጭብጥ በዚሁ እናበቃለን

ዳኛ/ ታደሰ/ :የ17ኛ ተከሳሽ መ/ምስክሮች በተመለከተ አቀራረባቸው እንዴት ነው? የሚመሰክሩበት ጭብጥ?

የ17ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ ሰለሞን ሃብቴ፡ ያው አጠቃላይ ያለን ጭብጥ ሁለት ነው አሁን ከመጡት ምስክሮች እና ይሄ መቀሌ ማረሚያ ቤት ያለው የተለየ ጭብጥ ነበር ያው ምንም ችግር አልነበረውም ያኛው ግን ከገጠር የመጣው ነው ከቀሩት ጋር የሚመሳሰል ጭብጥም አለው

ዳኛ/ ታደሰ/ ስንት ምስክሮች ናቸው የቀረቡት ዛሬ?

የ17ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ፡ አሁን ሁለት ናቸው የቀረቡት

ዳኛ/ ታደሰ/፡ በዚህ ጭብጥ አራት ምስክሮች ነበር ለማቅረብ የፈለጋችሁት ሁለት ቀርቧል የተቀሩት ሁለቱ የት ነው ያሉት?

የ17ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ፡ ያው ገጠር ናቸው ወደ ኮሮም አከባቢ ገጠር

ዳኛ/ ታደሰ/ ሁለቱ ኮሮም ነው ያሉት እዚህ የቀረቡት ሁለቱ አንዱ ማረሚያ ቤት ሆኖ አንዱ ከዝያ የመጣ ነው?

የ17ኛ ተከሳሽ ተ/ጠበቃ፡ አዎ ግን በወረዳ ነው የሚገናኙት እንጂ

ዳኛ/ ታደሰ/ ደህና አሁን የፈላጋችሁት ምንድንነው እናንተ?

የ17ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ፡ እንግዲህ ያው ፍርድ ቤቱ የሚፈቅድ ከሆነ የተለያየ ጊዜ ይቀርባሉ ካልሆነ ግን አጠቃላይ እንዲቀርቡ ነው የምንፈልገው ይሄ መቀሌ ማረሚያ ቤት ያለው ብቻም እንዲሰማ አንፈልግም፡፡

ዳኛ/ ታደሰ/፡ በድጋሚ ይረጋገጥና ተለዋጭ ቀጠሮ እንሰጣለን

1168

440

1110

የ17ኛ ተከሳሽ ተ/ ጠበቃ/ እሺ አመሰግናለሁ ክቡር ፍ/ቤት
ዳኛ/ ታደሰ/ ትእዛዝ እየተሰጠ ነው።

ት እ ዛ ዝ

በ3ኛ ተከሳሽ የመጡት መ/ምስክሮች አቶ ሃይሉ መሓሪ በደሞዛቸው መጠን የ2 ቀን አበል፣ እንዲሁም ወ/ሮ ባፊና ወልዱ ደግሞ የአንድ ቀን አበል እና አቶ ሃይሉ መሓሪ ከሳምሬ መቀሌ የትራንስፖርት ደርሶ መልስ በሚያቀርቡት ፋክቱር መሰረት እንዲሁም ወ/ሮ ባፊና ወልዱም ከኩሓ መቀሌ የትራስፖርት ደርሶ መልስ በሚያቀርቡት ፋክትር መሰረት ከ3ኛ ተከሳሽ ካስያዘው ገንዘብ እንዲከፈላቸው በዛሬው የ17ኛ ተከሳሽ መ/ምስክሮች ሁለት ምስክሮች ብቻ ናቸው የቀረቡት አንዱ ከማረምያ ቤት ነው አንዱግን አቶ ወልደሰንበት ከበደ የሦስት ቀን አበል እንዲከፈላቸው ከስላዋ የመጡበት ፋክቱር ካሳዩም የደርሶ መልስ ትራስንፖርት 17ኛ ተከሳሽ ካስያዘው ገንዘብ እንዲከፈላቸው ነው ፍ/ቤቱ የሚያዘው ያለው ሌላው በ7ኛ፣8ኛ እና 16ኛ ተከሳሾች ላይ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ቀጠሮ እንይዛለን ከዝያ በፊት ግን የ7ኛ ፣8ኛና 16ኛ ተከሳሾች ቅጣትን አስመልክቶ መፋረጃ ሃሳብ ከቀጠሮ በፊት እንድታቀርቡ ታዘዋል፣ ሌላው የ3ኛ ተከሳሽ መከላከያም ምስክሮች ለመስማት ነው ስለዚህ ቀጠሮ ለህዳር

18/1995 ዓ/ም።

ቀን 18/03/95 ዓ/ም

ዳኞች

ገብሩ ዘነበ

ታደሰ ሕሉፍ

አብርሃ መስለ

ከሳሽ ልዩ ዓ/ህግ ገብሩ ገበዬህ ቀርቧል

ተከሳሾች 3ኛ አቶ ገ/ስላሴ ካሳ ከጠበቃቸው ዘርአይ ግደይ ጋር ቀርቧል

5ኛ አቶ ነጋ አበባው ከጠበቃቸው ተሾመ አያሌው ጋር ቀርቧል

7ኛ መም/ር ብርሃነ ፀጋይ ከጠበቃቸው ንጉስ ሓጎስ ጋር ቀርቧል

8ኛ መም/ር ስለሞን አሰፋ ከ/ጠበቃቸው ተሾመ አያሌው ጋር ቀርቧል

16ኛ አቶ ገዛኢ ከበደ ከጠበቃቸው አለም ገ/እግዚአብሄር ጋር ቀርቧል

17ኛ አቶ ግርማይ ድንቃየሁ ከጠበቃቸው ተሾመ አያሌው ጋር ቀርቧል

18ኛአቶ ገ/ህይወት ወ/ገብርኤል ከጠበቃው በላይነሽ ወ/ስላሴ ጋር ቀርቧል

መዝገቡ ለዛሬው ቀን የተቀጠረው በ7ኛ፣ 8ኛ እና 16ኛ ተከሳሾች ላይ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠትና የ3ኛ ተከሳሽ ቀሪ መከላከያ ምስክሮች ለመስማት ነው:: አስቀድመን የቅጣት ውሳኔ እንደሚከተለው ሰጥተናል::

## ቅ ጣ ት

7ኛ ተከሳሽ መ/ር ብርሃነ ፀጋይ እና 8ኛ ተከሳሽ መ/ር ሰለሞን አሰፋ ጥፋተኞች የተባሉት ከግብረ አበሮቻቸው ጋር በመሆን መስከረም 3/1972 ዓ/ም በእንትጮ ከተማ የህወሓት አባል ወይም ተባባሪ ነው በሚል በቁጥጥራቸው ስር የነበረውን አቶ ገ/ሄር ኪዳኑን በዱላ ደብድበው በመግደላቸው የወ/መ/ሕግ ቁጥር 32/1/ሀ እና 281/ሀ/ ተላልፈው ስለተገኙ ነው:: በዚህ ጥፋተኛ ከተባሉ ደግሞ የቅጣት ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ቅጣት ሊወሰንባቸው ይገባል: ይህንን ለማድረግ የግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የቅጣት ሐሳብ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል::

ልዩ ዓ/ሕግ ጥቅምት 25/1995 ዓ/ም ለችሎቱ በቃል እንዳስመዘገበው ሁለቱ ተከሳሾች ከሌሎች ግብረአበሮቻቸው ጋር በመሆን ሟችን በአስተዳደር ቢሮ በማስገባት ከምሽቱ 4 7:00 ባለው ጊዜ ውስጥ በድብደባ አሰቃይተው እንዲሞት ያደረጉ ናቸው:: ይሄ ደግሞ ምን ያህል በሰው ልጅ ላይ ሊፈፀም የማይገባው ዘግናኝ ድርጊት እንደሆነ ያሳያል:: በተቃራኒው ደግሞ የተከሳሾች የወንጀል አፈፃፀም ባህሪ አደገኛ መሆኑን የሚያመለክት ስለሆነ ጥፋቱ ከባድ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ 8ኛ ተከሳሽ ይሄን ወንጀል በፈፀመበት ጊዜ የቀበሌው ሊቀመንበር ተረጋግጧል:: ስለዚህ በወ/መ/ሕግ ቁ 81/1/ለ/ መሰረት ቅጣት የሚከብድ ነው:: 7ኛ ተከሳሽም በተመሳሳይ ስልጣን ባይኖረውም የወንጀሉ አፈፃፀም ባህሪ ከባድ ስለሆነ ለጥፋታቸው የሚመጥን ከበድ ያለ ቅጣት እንዲወሰን በማክበር አመለክታለሁ የሚል ነው::

ተከሳሾች በበኩላቸው የቅጣት ሐሳብ በፅሑፍ አቅርበዋል::

7ኛ ተከሳሽ መ/ር ብርሃነ ፀጋይ ሕዳር 2/1995 ዓ/ም በፃፈው እንዳመለከተው፣ ከ1969 ዓ/ም እስከ 1970 ዓ/ም የህ.ወ.ሓ.ት አባል ሆኖ በማገልገል ላይ እያለ በቀይ ሽብር እስር ቤት በ1970 ዓ/ም ታስሮ ብዙ ስቃይ የደረሰበት መሆኑን ይህ ደግሞ ለደርግ ስርዓት የነበረው ጥላቻ የሚያመለክትለት እንደሆነ፣በ1977 ዓ/ም የህወሓት አባል ተብሎ በድጋሚ በመቀሌ ማእከላዊ ምርመራ ታስሮ የተሰቃየ መሆኑን፣በ1981 ዓ/ም ደርግ ከመቀሌ እንደለቀቀ በህወሓት ስር ተደራጅቶ በቅንነት ሲያገለግል የቆየ መሆኑን፣ ቀደም ሲል በደርግ በተደጋጋሚ ሲታሰር በመቆየቱና አሁንም በእስር

ቀን 18-03-95ዓ-ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ፡ ዲሞክራሲያዊ፡ ሪፐብሊክ፡ መንግስት፡
ለክልል፡ ትግራይ መቐለ፡ ፍ/ቤት፡
መቀሌ

የመ/ፍ/ቤት፡ ወ/መ/ቁ ------ 1/91
የፍ/ብ/ህ/ወ/መ/ቁ ----- 190/85

ጉዳዩ፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሥ/ ቁጥር 187(1)/መሰረት የቀረበ መጠይቅ

በከሳሽ፡ ሐዩ ዐቃቤ፡ ህግ

በተከሣሽ እኔ መምህር፡ ገብረሂወት ፀጋዬ መካከል፡ በነበረው የዘር፡ ማጥፋት፡ ወንጀል፡ ክርክር፡ ጉዳይ እኩር፡ ጠ/ፍ/ቤት፡ በዘመን 18/03/95ዓ/ም፡ በቃለ ው፡ ትዕዛዝ፡ የሰጠው፡ የቅጣት፡ ውሳኔ፡ በውሳኔው፡ ከሰጠን ላይ ቅር ስላተሰኘሁ፡ የይግባኝ መብቴ ተጠብቆ፡ ይግባኝ መዝገብ፡ በወቅቱ፡ ተገልብጦ፡ እንዲሰጠኝ፡ ሰል፡ በትህትና፡ አመለክታለሁ፡፡

አመልካች

የህግ፡ ታራሚ፡ መምህር፡ ገብረሂወት፡ ፀጋዬ

20/3/95

1172

ሚያዝያ 1 ቀን 1995 ዓ/ም

ለኢት/ፌዴ/ዴ/ሪፐ/መንግሥት
ከፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በፍትሐ ብሔር ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 486 መሠረት ስለሚቀርብ ቃለ መሃላ

ስም - ብርሃኑ ለገሰ ለማ

ዕድሜ - 51 ዓመት

ሥራ - የሕግ ተወካይ

አድራሻ - መቀሌ መርካቶ ቤት የሚከተሉትን ከዚህ በታች ቃለ መሃላ ፈፅሜያለሁ::

የቀን ገቢ - የለኝም

የወር ገቢ - የለኝም

የሚንቀሳቀስ ንብረት የለኝም

የማይንቀሳቀስ ንብረት የለኝም

የተጠቀሱት የሚከፈል ንብረት የለኝም ይህ የሆነ ከላይ ለተጠቀሱት የዳኝነት ዳኛ ለፍ/ቤቱ ከተጠቀሱት ስለ ለፍ/ቤቱ አመለክታለሁ::

ፊርማ የሕግ ተወካይ

ምስክሮች 1ኛ/ ሽምብሉ አስፋው ለገሠ ለርህ

2ኛ/ አቶ ካሳሁን ገ/ሕይወት አለሙ

3ኛ/ አቶ ፀሐዬ ገብሬ የሰጠን ከላይ አመልካች

የተጠቀሰው አመልካች የዳኝነት ዳኝነት ሊከፈለው የሚገባ ገንዘብ የለውም ይህ ዓይነት መሆኑን እናረጋግጣለን::

የምስክሮች ፊርማ

1

2

3

1173

ቀን፣ 13/08/95
የወ/መ/ቀ. 1/90

በኢ.ት/ፌደራላዊ ሪፑ/መንግስት
ለፌደራል ጠ/ፍ/ቤት
**አዲስ አበባ**

**ጉዳዩ፣ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር - 189/1/መሰረት ለቀረበ ይግባኝ ማስደገፊያ**

በይግባኝ ባይ - መም/ብርሃነ ፀጋይ በየነ እና

በመልስ ሰጪ - ልዩ ዐቃቤ ህግ መካከል በት/ክ/ፍ/ቤት በነበረው የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ክርክር ጉዳዩ፣ ክርክሩ ቀጥሎ ከቆዬ በኋላ የስር ውሣኔ ሰጪ ጠ/ፍ/ቤት በዐቃቤ ህጉ ለቀረበው ክስና ማስረጃ ብቻ ትኩረት በመስጠት የከሳሽ ምስክሮች በጭብጡ መሰረት ወንጀል ሲፈፅም አይተናል ብለው ሳይመሰክሩብኝ እና የእኔ የይግባኝ ባዩ አጥፊነት በህግ ፊት ሳይረጋገጥ እንዲሁም የእኔ የመከላከያ ምስክሮች ያረጋገጡትን ሃቅ ሚዛን በመንፈግ ያለበቂ ህጋዊ ምክንያት ጥፋተኛ ነህ በማለት በ18/03/95ዓ.ም በዋለው ችሎት በ13ዓመት ፅኑ እስራት እንድቀጣ ፈርድ ሰጥቷል:: እኔም ይህን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 185 እና 189/1/መሰረት ቅሬታዬን እነሆ ከዚህ ማመልከቻዬ ጋር አያይዤ አቅርቤያለሁ::

ለዚህ ይረዳ ዘንድ

| | |
|---|---|
| 1ኛ. ከስር ፍ/ቤቱ የተላከልኝ የመዝገብ ግልባጭ | 1170ገፅ |
| 2ኛ. የይግባኝ ቅሬታዬ የገለፅኩበት | 7ገፅ |
| 3ኛ. የነፃ ድህነት ማረጋገጫ ፎርም | 2ገፅ |
| በድምሩ | 1179ገፅ |

ከዚህ ማመልከቻዬ ጋር አባሪ በማድረግ የላኩኝ ሲሆን ክቡር ፍርድ ቤቱ የይግባኙ ፋይል በፅሞና መርምሮ ፍትሃዊ ውሳኔ ይሰጠኝ ዘንድ በታላቅ ትህትና አመለክታለሁ::

ይግባኝ ባይ
የህግ ታራሚ ብርሃነ ፀጋይ በየነ

[redacted]

1175

- የከሳሽ ምስክር ሆነው የቀረቡት 17ኛ ምስክር መም/ ለማ ሃይለ ራሳቸው በምርመራ ተግባር ተሳታፊ ሆነው ሳለ ከሳሹን መስሪያ ቤት አሳስተው ራሳቸውን ለማዳን ሲሉ ከነበረው ሁኔታ በራቀ መልኩ የመሰከሩ ለመሆናቸው፣
- በወቅቱ በጥበቃ ስራ ሆነው ሁኔታውን በትክክል በተገነዘቡ የእኔ የመከላከያ ማስረጃ ተረጋግጠባቸዋል::

5.2. 18ኛ ምስክር ሆነው የቀረቡት አቶ አስገዶም ምህረት፣ በ30/01/72ዓ.ም በእንትጮ ወረዳ አስተዳደር ቢሮ በጥበቃ ስራ ላይ ነበርኩ ያሉት ሓሰት መሆኑን በዚህ እለት በአቶ ወልዱ ረዳ ቤት እንዳደሩ ስለሟቹ አሟሟት የሰሙት ግት በመምህር ብርሃነ መብራሁቶም አማካኝነት ተጠርተው እንደነበረ ተመስክሮባቸዋል:: እሳቸው ግን ከጋብቻ ዝምድናቸው የተነሳ በባለቤታቸው ጉትጎታ ለብቀላ ሲሉ ሁኔታዎችን አደበላልቀው ያላዩትን አስመስለው ለመናገራቸው ተረጋግጠባቸዋል::

5.3. 19ኛ ምስክር ሆነወ የቀረቡት አቶ ታደሰ ፍስሃ የተባሉት በእለቱ ከአቶ ጉሩም አስፍሃ ጋር በእስር ቤት አብረው ታስረው እንደነበረ ተመስክሮባቸዋል::
- እሳቸው ግን ይህን ክደው በሐሰት ለመመስከራቸው መዝገቡ ያስረዳል::

5.4. በጠቅላላ 3ቱም የከሳሽ ምስክሮች በተለይ እኔን የአሁኑ ይግባኝ አቤቱታ አቅራቢ በተመለከተ በአንድ ቃል፣
- ስራዬ መምህርነት እንጂ ሌላ ስራ እንዳልነበረኝ አረጋግጠው መስክረዋል፣
- ይህም እውነት ከሳሹ በክሳቸው ላይ የፖለቲካ እስረኛ መርማሪ ሲሉ የሰየሙትን ስያሜ ሐሰትነት ያረጋግጣል፣
- በመቀጠልም 3ቱም የሟቹ ገዳይ ማን መሆኑን በዓይናቸው እንዳላዩ መስክረዋል፣
- በሩ ተዘግቶ ስለነበረ ሟቹ ፲አለቃ አባይ አጉል ቦታ መታኸኝ ብሎ ሲናገር ብቻ መስማታቸውን መስክረዋል::

5.5. ስለዚህ እኔ በቦታው ያለመኖሬን በበቂ ሁኔታ ከመከላከሌም በላይ በከሳሽ ማስረጃም ቢሆን በቦታው ሲገባ ነበረ ከማለት ያለፈ ወንጀል ስለመፈፀሜ የቀረበ ማረጋገጫ የለም:: በዚህ ሁኔታ መሰረት የኢት/ወ/መ/ህግ ቍጥር 23/2/3 በተመለከተው መሰረት የወንጀል ድርጊት በእኔ ለመፈፀሙ የቀረበ እውነተኛ የማረጋገጫና የዓይን ማስረጃ የለም::

6. የጥፋተኝነት ውሳኔ በተመለከተ፣
- ከላይ በዝርዝር የከሳሽ ማስረጃና የእኔ የተከሳሽ መከላከያ በማገናዘብ እንዳቀረብኩት ሁሉ፣
- የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከሳሽ ምስክሮች የጋብቻ ዝምድና፣ እንዲሁም ከተጠያቂነት ለመዳን የተደረገ ተንኮል ለመኖሩ በቀረበለት የምስክሮች ቃልና የመከላከያ ሁኔታ ተገንዝቦ ሳለ፣
- የምስክሮችን የቃል አሰጣጥ ልዩነትና ግምት ሳይሰጥ፣
- በተለይም ለመከላከያ ምስክሮቹ ትኩረትና ሚዛን በመንፈግ ሙሉ በሙሉ የከሳሽን ክስ እንዳለ በመቀበል፣ ወንጀል ያልፈፀምኩ ለመሆኔ ተረጋግጦ ሳለ፣

1177

- ለኢት/ወ/መ/ህግ ቁጥር 23/2/3 ወይም በዚሁ ግን ቁጥር 34 የተመለከተውን በማለፍ የኢት/ወ/መ/ህግ ቁጥር 24 መሰረት ምክንያትና ውጤቱን ባለማመዛዘን የጥፋተኝነት ውሳኔ በእኔ ላይ ስለሰጠ ክቡር የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ ያስከተለው የህግ ስህተቱን በማረም ውሳኔውን እንዲሰርዝልኝ አመለክታለሁ::

7. የቅጣት ውሳኔ በተመለከተ፣

3.2. 18ኛ የከሳሽ ምስክር አቶ አስገዶም ምህረት የሰጡት ቃል ፍሬ ነገር ባጭሩ፣

- መስከረም 02/1972ዓ.ም ሟች አቶ ገ/እግዚአብሔር ኪዳኑ በእንትጮ ከተማ ውለው መስከረም 03/72ዓ.ም ታስረው ማታ በእንትጮ ወረዳ አስተዳደር ቢሮ ውስጥ ሲመረመሩና አስቀድመው ወደ ቢሮው የገቡት ፲አለቃ አባይ፣ የማን ተኸሊት፣ መም/ ብርሃነ ፀጋይ እንደነበሩና ለሟች ገ/እግዚአብሔር ኪዳኑ ግን የ፲አለቃ ጫካ አለማየሁና የማን ተኸሊት ይዘዋቸው ወደቢሮው በመግባት ወንድምህ ጠአመ ኪዳነ ቤትህ አሳድረሃል እያሉ መደብደብ እንደጀመሩ ሟቹም አላሳደርኩም ከወንድሜ ጋርም ግንኙነት የለኝም እባካችሁ አትግደሉኝ ይሉ እንደነበር ገልፀዋል::
- በተጨማሪም የ፲አለቃ አባይ ገ/ህይወት ስም በመጥቀስ አባይ በማይሆን ቦታ መታኸኝ እያሉ ሟቹ ከምርመራ ክፍል ደግፈው በማምጣት ለእነ አስገዶም ምህረቱ አስረከብዋቸዋል:: እነሱም ተረክበው እስር ቤት እንዳስገቡዋቸው በዚህ ቀን ሌሊት በ8ሰዓት ስዒድ የተባለው፣ ሰውየው እኮ ሞቷል ሲል የነገራቸው መሆንን መስክረዋል::
- ሟቹ ሲመረመሩ በሩ ተዘግቶ ስለነበረ ሟቹን ማን እንደገደላቸው አለማየታቸውን ነገር ግን በድምፅ አባይ ምን አለበት በአንድ ጥይት ብትገድለኝ እያሉ ሲጮሁ መስማታቸውን መስክረዋል::
- እኚህ ምስክር ከሟች ጋር የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ለመሆኑ ተናግረዋል::

3.3. 19ኛ የከሳሽ ምስክር አቶ ታደሰ ፍስሃ የሰጡት ቃል ፍሬ ነገር ባጭሩ፣

- ሟቹ መስከረም 2/1972ዓ.ም በዓል አክብረው ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ትጠራለህ ተብለው ተጠርተው እንትጮ ወረዳ አስተዳደ ቢሮ ድረስ መጡ:: በነጋታው መስከረም 3/72ዓ.ም ወንበዴው ወንድምህን አሳድረሃል ተብለው ተደበደቡ::
- የወረዳው አስተዳደሪ ፲አለቃ አባይ ገ/ህይወት ሲሆን የተደበደቡትም በአስተዳደሩ ቢሮ ውስጥ ነበረ ብሏል::
- ሲደበደቡ የነበሩ ፲አለቃ አባይ፣ የማን ተኸሊት ነበሩ መም/ ብርሃነ ፀጋይም ገቡ ትንሽ ቆይቶም ገ/ፃድቃን፣ መም/ ሰለሞን ገቡ::
- ወንድምህ ጠአመ ኪዳኑ በቤትህ አሳድረሃል ተብለሃል እመን እያሉ ይደበድቡዋቸው ነበረ፣ ሟቹ ግን አላየሁም እንዲያውም አንግባባም ይሉ ነበር፤ ከዚያም ፲አለቃ አባይ አንድ ግዜ አናግረኝ አሉት እሺ ተናገር አላቸው እሳቸውም ከወንድሜ ጋር ፍቅር የለኝም ሲሉ በሉት አሁንም እየተዋጋን ነው አላቸው::
- ፲አለቃ አባይ በጫማ በማይሆን ቦታ መታኸኝ እንግዲህ አገሩ ይስፋልህ አሉት፣ ፲አለቃ ጫካ፣ የማን፣ መም/ብርሃነ ፀጋይ ተቀበሉት አሉን ህይወቱ አላለፈም ነበረ::
- ከዚያ አንድ ሰው ይህ ሰው ደክመዋል አለኝ፣ አባይነሽ የምትባል ሴት አባይ ሄደሽ እይው አላት፤ እሷም ህይወቱ እንዳለፈ ለአባይም ለእኔም ነገረችኝ ከዚያ ገብተን የአቶ አስገዶም ጋቢ ሸፈንናቸው ለአባይም ሬሳውን እንድወስደው ለመንኩት፣ ፲አለቃ አባይም ቤተክርስትያን ለመቅበር አይፈቀድም አለኝ ወስደን በረሃ ቀበርናቸው ብሏል::
- ከሟቹ ጋር የጋብቻ ዝምድና አለኝ ብሏል::
- የመምህር ብርሃነ ፀጋይ ስራ መምህርነት መሆኑን አውቃለሁ ብሏል::
- የመመርመሪያ ቢሮ ዝግ ነበረ ለእኔ አይታየኝም ድምፅ የሚሰማው ግን የ፲አለቃ አባይና የሟቹ ብቻ ነበረ ብሏል::

## 4. የተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ይዘትና ፍሬ ነገር ባጭሩ፣

1179 4.1. 1ኛ. የመከላከያ ምስክር አቶ ኪዳነ ማርቆስ የሰጡት ቃል፣

- የመም/ ብርሃነ ፀጋይ ስራ መምህርነት ብቻ መሆኑን አውቃለሁ ብሏል:: ሌላ ተጨማሪ ስራ የላቸውም በማለት አረጋግጠው፣ አስረድተዋል::
- እኚህ የመከላከያ ምስክር መስከረም 3/72ዓ.ም በእንትጮ ወረዳ አስተዳደር ቢሮ ግቢ ውስጥ በዘብ ጥበቃ ስራ ማደራቸውን ገልፀው፣

11826

ሰኔ 10 ቀን 1995 ዓ/ም

[illegible]
[illegible]

ጉዳዩ፡ ክስ፡

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

13/10/95

1182

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
FEDERAL SUPREME COURT

ቀን 28-11-95
Date
ቁጥር 11826
Ref. No.

ለ-[illegible]
[illegible]

በይግባኝ ባይ [illegible] እና

በመልስ ሰጭ [illegible] መካከል ባለው

[illegible] ወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት

ወ/ችሎት ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል::

ስለዚህ ለመልስ ሰጭ መድረስ የሚገባውን መጥሪያና የይግባኝ ቅሬታ ማመልከቻ 6-- ገጽ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ስለሆነ ለመልስ ሰጭ በእናንተ በኩል ደርሷቸው መልሳቸውን ይዘው ለ-[illegible] ቀን 1996 ዓ.ም. ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ወ/ችሎት ከጥዋቱ 2:30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል::

30/11/95

1183

ስልክ Tel. 55 34 00 ፋክስ Fax 550278 114793 ፖ.ሣ.ቁ. P.O Box 6166 አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

ንግድ ማተሚያ ድርጅት

በአጠቃላይ የይግባኝ ባይ የመከላከያ ምስክሮች የመልስ ሰጪን ቀጥተኛ ምስክሮች አላስተባበሉም ። ስለሆነም ይግባኝ ባይ ተቃውሞ ውድቅ እንዲሆን እንጠይቃለን ።

ይግባኝ ባይ ወንጀሉን አለመፈጸሜን ባስረዳም የ13 ዓመት የእስራት ቅጣት ተፈር በኛል ። ስለዚህ ይህ የፍርድ ቅጣት ያለአግባብ የተወሰነ ስለሆነ ክቡር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፍርዱን በኢት/ወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.195/ለ/1/ በተመለከተው መሠረት በነጻ እንዲያሰናብተን በትህትና አመለክታለሁ በማለት ተከራክረዋል ።

ይግባኝ ባይ ወንጀሉን አለመፈጸማቸው በመልስ ሰጪ ምስክሮች ተረጋግጧል ። በአቀረቧቸው የመከላከያ ምስክሮችም የወንጀል ድርጊቱን ያለመፈጸማቸውን አላስተባበለም። ከወንጀሉ ክብደት አንጻር በይግባኝ ባይ ላይ የተጣለው የ13 ዓመት የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚያንስ እንጂ የሚበዛ አይደለም ። ያቀረቡአቸው የቅጣት ማቅለያ ሃሳብም በወ/መ/ሕ/ የተሸፈኑ አይደሉም ።

<u>ማጠቃለያ</u>

ይግባኝ ባይ በቀረበባቸው ክስ ወንጀል የፈጸሙ መሆኑ በመረጋገጡ ፤ ባቀረቡአቸው ምስክሮች ይህንን ያላስተባበሉ በመሆኑ ፤ የተጣለባቸውም ቅጣት ከወንጀሉ ክብደት አንጻር ተገቢ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንዲያጸድቀው በትህትና እንጠይቃለን ።

1184

የመከላከያ ምስክር የሆኑት መምህር ብርሃነ መብራቶም እና ሚች ገ/እግዚአብሔርን ከሌሎች አራት ግለሰቦች ጋር በመሆን ወደ ምርመራ ክፍል የወሰዱት አቶ ለማ ሃይሌ መሆናቸውን መስክረዋል ። ይግባኝ ባይም በቦታው እንዳልነበርኩ መስክረዋል ። የመከላከያ ምስክር የሆኑት አቶ ግሩም አስፍሃ ይግባኝ ባይ ሚች ሲመረመረር በቦታው አለመኖሬን ገልጸዋል ። አራተኛ እና አምስተኛ ምስክሮች ይግባኝ ባይ በ03/01/72 በቤታቸው ማደራቸውን ገልጸዋል ።

በአጠቃላይ የመከላከያ ማስረጃዎቹ የመልስ ሰጪ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ለማ ኃይሌ በክሱ የወንጀል ድርጊት ተሳታፊ መሆናቸውን እና እራሳቸውን ለማዳን የተሳሳተ መረጃ መስጠታቸው ተረጋግጧል ። የመልስ ሰጪ 18ኛ ምስክር ሆነው የቀረቡት አቶ አስገ ም ምህረት በ03/10/72 በቦታው እንዳልነበሩ ተረጋግጧል ። እኝህ ምስክር የሚች ዘመድ ስለሆነ ለብቀላ ይግባኝ ባይን ለመጉዳት የሰጡት ምስክርነት ቃል ነው ። አቶ ታደሰ ፍሰሃ የተባሉት 1ኛ የመልስ ሰጪ ምስክር ከአቶ ግሩም አሰፋ ጋር በእስር ቤት አብረው መታሰራቸው ተረጋግጧል ። ስለዚህም የሰጡት የምስክርነት ቃል ተአማኒነት የለውም። በማለት ተከራክረዋል ።

ይግባኝ ባይ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው የመከላከያ ምስክሮች የመልስ ሰጪ ምስክሮች የሰጡትን ቃል አላስተባበለም ። እርስ በርሱ የተምታታ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ነው ። የመልስ ሰጪ ምስክሮች ግን ቀጥተኛ ማስረጃ ናቸው ። የመዝገቡ ዝርዝር እንደሚያመለክተው የይግባኝ ባይ የመከላከያ ምስክሮች በተጠና መልኩ ቀርበው ፣ የሥር ፍ/ቤትን ለማሳሳት የሞከሩ ናቸው ። ቀጥተኛ ማስረጃን ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ሊያስተባብል አይችልም ። ይግባኝ ባይ የመልስ ሰጪ አስራ ሰባተኛ ምስክር ለማ ሀይሌ የወንጀሉ ተሳታፊ ስለሆነ የተሳሳተ ምስክርነት ሰጥተዋል በማለት ያቀረቡት ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ነው ። ይህንንም መከላከያ ምስክሮች ከዚህ አኳያ የሰጡት ቃል እርስ በርሱ መጋጨቱን በጉልህ ያረጋገጠ ነው ።

ይግባኝ ባይ በቦታው አለመኖሬን የመከላከያ ምስክሮች አስረድተዋል ቢሉም የመልስ ሰጪ ቀጥተኛ ምስክሮች ይግባኝ ባይ በቦታው መኖራቸውን አረጋግጠዋል ። ይግባኝ ባይ ምርመራ ክፍል ውስጥ በማንኛውም ሰዓት ሊገቡ ይችላሉ ። በዚሁም ምክንያት መከላከያ ምስክሮቹ ድርጊቱን ሊያስተባብሉ ወይም ሊያረጋግጡ አይችሉም ። አራተኛ እና አምስተኛ የመከላከያ ምስክሮች ይግባኝ ባይ በ03/01/72 በቤታቸው ማደራቸውን አረጋግጠዋል በማለት ይግባኝ ባይ ገልጸዋል ። ነገር ግን የሁለቱ ምስክሮች ቃል ፈጸሞ ተአማኒነት ሊኖረው አይችልም ። ለዚህ ዋናው ምክንያት ይግባኝ ባይ በማንኛውም ሰዓት ከቤታቸው ውጪ ሊያድሩ ይችላሉ ። ይህንን መከላከያ ምስክሮቹ ሊያስተባብሉ ወይም ሊያረጋግጡ አይችሉም ። በተለይ መከላከያ ምስክሮቹ በስር ፍ/ቤት የሰጡት እርስ በርሱ የተጠረዘ የምስክርነት ቃል በተጠና መልክ ፍ/ቤትን ለማሳሳት የተሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል ።

1185



የልዩ ዐቃቤ ሕግ ሹም

1.2 ይግባኝ ባይ "የከሳሽ ልዩ ዐቃቤ ሕግ (መልስ ሰጪ) የሰው ማስረጃ ይዘት" በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር የሚከተለውን መከራከሪያዎች አቅርበዋል ::

- መልስ ሰጪ የሚከተሉትን ሶስት ምስክሮች አቅርቧል :: እነዚህም መምህር ለማ ኃይል ፣ አቶ አስገዶም ምህረት ፣ አቶ ታደሰ ፍሰሃ ናቸው :: ሶስቱም ምስክሮች በተመሳሳይ መልኩ ነው የመሰከሩት :: ይኸውም መስከረም 3/1972 ዓ.ም በእንትጬ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ቢሮ ውስጥ የወረዳው ኃላፊ ፲/አ አባይ ገ/ሕይወት ፣ የፖሊስ አዛዥ ፲/አ ጫካ አለማየሁ ፣ የማነ ተክሊት ሆነው ሲገቡ መምህር ብርሃን ፀጋይ (ይግባኝ ባይ) እና መምህር ሰለሞን አሰፋ አብረው ነበሩ ፤ በማለት ነው ::

- ሶስቱም ምስክሮች መምህር እንደሆንኩ መስክረዋል :: ሶስቱም ምስክሮች ሟችን ማን እንደገደለው አላዩም :: መምህር አስገዶም ምህረት የሟች ዘመድ ነው ፤ በማለት አስረድተዋል ::

ይግባኝ ባይ የመልስ ሰጪ ምስክሮች ለሥር ፍ/ቤት የሰጡትን ቃል በቁንስል ነው ያቀረቡት :: በተለይ መምህር አስገዶም የተባሉት ይግባኝ ባይ ሟች ገ/እግዚአብሔር ኪዳኑ ይግባኝ ባይን ጨምሮ ሌሎች ግብረአበሮቻቸው ጋር በመሆን ሟችን ከተደበደቡ በኋላ ወደ እስር ቤት ወስደው እንዳስረከቧቸው አረጋግጠዋል :: የመልስ ሰጪ ምስክሮች ሟች በሚደበደብበት ወቅት ይግባኝ ባይ በምርመራ ክፍል ውስጥ ነበሩ :: ይግባኝ ባይ በዚህ ክፍል ውስጥ የነበሩት ሟች ሲደበደብ እያዩ ለመደሰት አሊያም ለማዘን ነው ሊባል አይቻልም :: ይግባኝ ባይ ሟች ላይ በደረሰበት ድብደባ እናም ሞትን ባስከተለበት ድርጊት ሙሉ በሙሉ ተባባሪ ነበሩ :: መምህሩ አስገዶም ምህረት የሟች የጋበቻ ዘመድ መሆኑ ብቻ የሰጠውን የምስክርነት ጥርጣሬ ውስጥ አያስገባውም :: ምስክሩ በወቅቱ እስር ላይ በነበሩበት ወቅት ነው ድርጊቱን የተመለከቱት :: የሳቸውም ቃል በሌሎች የመልስ ሰጪ ምስክሮች ተደግፎአል ::

1.3 "የተከሳሽ የመከላከያ ይዘት" በሚለው ንዑስ አርእስት ይግባኝ ባይ የሚከተለውን አስፍረዋል ::

አምስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቤ አሰምቻለሁ :: አንደኛ የመከላከያ ምስክር አቶ ኪዳኑ ማረቆስ ይግባኝ ባይ መምህር መሆኔን አስረድተዋል :: ሟች ገ/እግዚአብሔር ምርመራ በተካሔደበት የአስተዳደር ክፍል ሲገባ በቦታው እንዳልነበርኩ አስረድተዋል :: ከዚህ ይልቅ የመልስ ሰጪ (ልዩ ዐቃቤ ሕግ) ምስክር የነበረው ለማ ኃይሌ ሟችን ወደ ምርመራ ክፍል ይዞት እንደገባ ድብደባው ከተፈጸመም በኋላ ይዞት እንደወጣ ገልጸዋል፤ በማለት አስፍረዋል ::

1186



አየለ ሞገስ
ዳኛ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ሹም

ስለሆነም ማስረጃ ሳይኖር በዘፈቀደ የተበየነብኝ ስለሆነ ክቡር ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ በሥር ፍ/ቤት ያቀረብኩትን የክስ አመሰራረትና ጉድለት በተመለከተ የቅድመ ክስ ክርክር መቃወሚያዬን በቂና ህጋዊ ግምት ሳይሰጥ ቀርቶ የሰጠውን ብይን ውድቅ እንዲያደርግልኝ በትህትና አመለክታለሁ ፤ የሚል መከራከሪያ ይግባኝ ባይ አቅርቧል ::

ሆኖም ይግባኝ ባይ የተከሰሱበት ወንጀል ማለትም ገ/እግዚአብሔር ኪዳኑን የህወሃት አባል አሳድረሃል በማለት በምርመራ ወቅት ባደረሱበት ድብደባ በመሞቱ ምክንያት ነው ::

ይግባኝ ባይ እና ግብረአበሮቹ ሟችን ለሞት የሚያደርስ ድብደባ ያደረሱበት የህወሃት አባል ነህ በማለት ነው :: ከዚህም መረዳት የሚቻለው ሟች የፖለቲካ አቋሙ የተለየ ሰው አሳድረሃል በሚል ግምት መገደሉን ነው:: ስለዚህም ህወሃት የፖለቲካ ድርጅት ነው :: በነሲብ ግምት ላይ ተመስርተው አሰቃቂ ድብደባ ፈጽመው ከሞተ በኋላ የህወሃት ደጋፊ ስለሆነ ጫካ ጣሉት ተብሎ አስክሬኑ በክብር ቤተክርስቲያን እንዳያርፍ በበርሃ ተወርውሯል:: እነዚህ ተግባሮች መፈጸማቸውም በመልስ ሰጪ ምስክሮች በሚገባ ተረጋግጧል:: ወንጀሉ የተፈጸመውም የመንግስትን መዋቅር በመጠቀም ፤ በመንግስት ኃላፊዎች ፤ ሰላማዊ በሆኑ ዜጎች ላይ ነው :: የወንጀሉ ተግባሩም ከወቅቱ በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለየ አመለካከት አለው ተብሎ የሚጠረጠር ግለሰብን ለማጥፋት የሚደረገው ዘመቻ አካል ነው :: ስለዚህም መልስ ሰጪ (ልዩ ዐቃቤ ሕግ) የወ/መ/ሕ/ቁ.281/1/ሀ/ በመጥቀስ በይግባኝ ባይ ያቀረበው ክስ ተገቢ ነው ::

መልስ ሰጪ ለወ/መ/ሕ/ቁ.281/1/ሀ/ በአማራጭ የወ/መ/ሕ/ቁ.522 /1/ሀ/ለ/ መጥቀሱ አግባብ ነው :: ለዚህ ምክንያቱ በሁለቱም አንቀጾች የተካተተው የወንጀል ድርጊቶች እና አፈጻጸሞች ተመሳሳይ ናቸው :: የሁለቱንም የወንጀል ድርጊቶች ለማስረዳት የሚያዘው ጭብጥ እና የሚቀርበው ማስረጃ ተመሳሳይ ነው :: ስለዚህም የይግባኝ ባይን የመከላከል መብት አያጣብብም ፤ ስለሆነም የይግባኝ ባይ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ተቃውሞ አላግባብ ነው ::

ይግባኝ ባይ የፖለቲካ እስረኛ መርማሪ በመባል የቀረበው ማስረጃ ያልተደገፈ ነው :: በሙያ መምህር ነኝ :: በማለት ተከራክረዋል :: መልስ ሰጪ መምህር አልነበሩም አላለም፤ ነገር ግን ሟችን ምርመራ ክፍል ውስጥ አስገብተው መርምረዋል :: ይህም በማስረጃ ተረጋግጧል :: የይግባኝ ባይ ክርክር ለመፈጸማቸው ከተረጋገጠው ወንጀል ጋር አግባብነት የለውም :: ስለዚህም ውድቅ እንዲደረግ እንጠይቃለን ::



አየለ ሞገስ
የልዩ ዐቃቤ ሕግ ሹም

Federal Democratic Republic of Ethiopia Office of the Special Public Prosecutor

1187

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Office of the Special Public Prosecutor

ቀን 10-2-96
Date
ቁጥር ጠ-6/028/96/92
Ref. No.

በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ወንጀል ችሎት
አዲስ አበባ

የወ/መ/ቁ.11820
የልዩ ዐ/ሕግ የወ/መ/ቁ.190/85

ይግባኝ ባይ :- ብርሃነ ፀጋዬ በየነ /መምህር/

መልስ ሰጪ :- ልዩ ዐቃቤ ሕግ

ጉዳዩ :- ይግባኝ ባይ ሚያዝያ 13 ቀን 1995 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የተሰጠ መልስ ፤

1. የይግባኝ ቅሬታው ባጭሩ እና የመልስ ሰጪ መልስ

1.1 ቅድመ ክስ ክርክርን በተመለከተ ከይግባኝ ባይ የቀረበ ቅሬታ

- መልስ ሰጪ (ልዩ ዐቃቤ ሕግ) በመሰረተው ክስ የጠቀሰብኝ የኢ/ወ/መ/ህ/ ቁ.281(32)(1)(ሀ)ን ነው ። ይግባኝ ባይ የተከሰስኩበት ወንጀል በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን የወንጀል ዝርዝሮች ስለማያሟላ የሥር ፍ/ቤት ያቀረብኩትን ተቃውሞ ውድቅ ያደረገው ያለበቂ ህጋዊ ምክንያት ነው ። ስለዚህ በሥር ፍርድ ቤት በወ/መ/ሕ/ቁ.281 /32/1/ሀ/ ጥፋተኛ መባሌ አላግባብ ነው ። መልስ ሰጪ (ልዩ ዐቃቤ ሕግ) የዘር ማጥፋት ወንጀል መፈጸሜን አላስረዳብኝም ። የፖለቲካ መርማሪ በመባል የቀረበውም ማስረጃ ያልተደገፈ ሀሰት ነው ፤ በሙያ መምህር ነኝ የሚል ነው ።

- በአማራጭ የቀረበብኝ ክስ የወ/መ/ሕ/ቁ.522/32/1/ሀ/ለ/ መሠረት በማድረጉን በተመለከተ ያቀረብኩት መቃወሚያ የሥር ፍ/ቤት ውድቅ ያደረገው ያለበቂ ምክንያት ዝርዝር እና ህጋዊ ትንታኔ ሳይሰጥ ነው።

አያሌ ጥጋብ
የልዩ ዐቃቤ ሕግ ሹም

1188

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
FEDERAL SUPREME COURT

ቀን 12-2-96
Date
ቁጥር 11826
Ref. No.

ለመቀሌ ማረሚያ ቤት

<u>መቀሌ</u>

በይግባኝ ባይ መም/ብርሃን ፀጋዬ በየነ እና በመልስ ሰጭ ልዩ ዓቃቤ ሕግ መካከል ስላለው ዘር ማጥፋት ወንጀል ጉዳይ ዓቃቤ ሕግ በ10/2/96 ዓ.ም የሰጠውን መልስ 5 ገጽ ከዚህ ጋር እየላክን ለይግባኝ ባዩ እንዲደርሰውና የመልስ መልስ የሚሰጥ ቢሆንም መልሱን ለህዳር 22 ቀን 1996 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 2:30 ሰዓት እዲያቀርብ ፍ/ቤቱ አዟል።

12/2/96

ሐብታሙ ፎርቂ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ም/ሬጅስትራር

1189

ስልክ Tel. 55 34 00
ፋክስ Fax 550278 114793
ፖ.ሣ.ቁ. P.O Box 6166
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

ንግድ ማተሚያ ድርጅት

## ክቡር ይግባኝ ሰሚ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት

ከዚህ በታች በሚቀርባቸው የቅጣት ማቅለያ ሃሳቤን ሳቀርብ ይህንኑም በሐዘኔታ እንደሚቀበለኝ ፍ/ቤቱ ቅንጣትም ያህል አልጠራጠርም፡፡

1ኛ - እኔ የአሁኑ ይግባኝ ባይ መልስ ሰጪ ቀደም ሲል በምንም መልኩ በወንጀል ተከስሼና ተቀጥቼ የማላውቅ ሰላማዊ የሃገሪቷ ዜጋ ለመሆኔ ቀደም ብሎ ያቀረብኩትን የቅጣት ማቅለያ ሃሳብ ፅሑፍ ከዋናው የፍ/ቤቱ መዝገብ ተያይዞ ይገኛል፡፡

2ኛ - ከዚህም በላይ እኔ በደርግ ዘመነ መንግስት የወያኔ አባል ነህ ተብዬ ከፍተኛ ችግር፣ እስራት፣ ግርፋትና እንግልት የተፈፀመብኝና 7 ዓመት ተወስኖብኝ ብዙ የተሰቃየሁ መሆኔን ለዚሁም ማስረጃዬ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡

3ኛ - አሁን በእስር ላይ እያለሁም ያልተማሩ የህግ ታራሚዎችን በማስተማር ተገቢ እገዛ እያደረግኩ ስለመሆኔ የተሰጠኝ ማስረጃ ከዋናው የፍ/ቤቱ መዝገብ ተያይዞ ይገኛል፡፡

4ኛ - በደርግ ስርዓት ይደርስ የነበረውን ግፍና ሰቆቃ ስርዓቱን በመቃወም ወደ ትግል ሜዳ ወጥቼ ከህወሃት ድርጅት ጋር በመቀላቀል በትጥቅ ስታገል ቆይቼ ከትጥቅ ትግል በኋላም ህወሃት በመደበኝ የስራ ቦታና ሃላፊነት ለ10 ዓመታት ያህል በትግራይ ክልል በሬድዮ ጋዜጠኝነት ሞያ ተመድቤ ከእኔ የሚፈለግብኝ የስራ ግልጋሎት አበርክቻለሁ፡፡ ይህም ቀደም ብዬ ባቀረብኩት የቅጣት ማቅለያ ፅሑፍ በዝርዝር ሰፍሮ ከዋናው መዝገብ ተያይዞ ይገኛል፡፡

5ኛ - እኔ በስራ በነበርኩበት ግዜ የሁለት/2/ ሚቾች ወንድሞቼን ልጆችና ከእኔ አብራክ የተወለዱትን 10 ልጆች በማስተማር ላይ የነበርኩ ሲሆን እኔ በመታሰሬ ምክንያት እነዚህ የማስተምራቸው የነበሩ ልጆች የሚያስተምራቸውና የሚጧራቸው አጥተው ትምህርታቸውን አቋርጠው የጎዳና ተዳዳሪ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ሌላም ወላጅ እናቴም ለ10 አመታት ያህል በበሽታ ታማ የአልጋ ቁራኛ የሆነችውን የሚጦራት አጥታ የጎረቤቶች እጅ እያየች ትኖራለች፡፡

## ክቡር ይግባኝ ሰሚ ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት

እኔ ይግባኝ ባይ ካቀረብኩዋቸው መ/ምስክሮች በሰጡት ኡነተኛ ምስክርነት በልዩ ዐ/ህግ ለተሰጠው ምስክርነት በሚገባ ተከላክዬ ያፈረስኩት መሆኑን በመግለፅ የመጀመሪያ ደረጃ የስር ፍ/ቤት በእኔ ላይ በ13 ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት የጣለብኝን ክቡር ይግባኝ ሰሚ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁጥር 195/ለ/1/ በሚያዘ ደንብ መሰረት ውድቅ አድርጎ በነፃ እንዲያሰናብተኝ አመለክታለሁ፡፡

አልያም በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቍጥር 185/ለ/ በመጥቀስ ያቀረብኩትን የቅጣት ማቅለያ ሃሳቤ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የስር ፍ/ቤቱ የጣለብኝን የ13 ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣቱን ዝቅ በማድረግ እንዲቀንስልኝ ስማፀን ይህንኑ ሳይሆን የሚቀር ከሆነ ግን በወ/መ/ህ/ቁጥር 195-196 ላይ በተደነገገው መሰረት ቅጣቱን በገደብ ገድቦ እንዲለቀኝ ስል በታላቅ ትህትና የመቃወሚያ መልሴን አቀርባለሁ፡፡

የመቃወሚያ መልስ አቅራቢ
የህግ ታራሚ መምህር ብርሃኔ ፀጋይ በየነ

ብርሃኔ ፀጋዬ



1190

## 1.5 የልዩ ዐ/ህግ ይግባኝ ባይ በማንኛው ሰዓት ከቤታቸው ውጪ ሊያድሩ ይችላሉ ለሚለውም፣

1.8. በመሰረቱ የልዩ ዐ/ህግ አባባል ከመሰረቱ ክሱ ውጭ በሆነ መንገድ የሄደ ይመስለኛል:: ይኸውም በማንኛውም ሰዓት ከቤታቸው ውጭ ሊያድሩ ይችላሉ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እኔ ከቤቴ ወጥቼ በውጭ አድሬ አላውቅም:: ይሁንና የቤተሰብ ሰርግ ወይም ሃዘን በሚያጋጥምብኝ ጊዜ በሰርግ ቤት ወይም በሃዘን ቤት ባድር ከተከሰስኩበት ወንጀል ጋር በምንም መልኩ ግኑኝነት ሊኖረው ይችላል? ይህንኑ አባባል ዋጋ የሌለው በመሆኑ ብዙውም መልስና ማብራሪያ ሳያስፈልገው ለማለፍ ተገድጄአለሁ ብልም ስህተት አይሆንብኝም::

## 1.6 የልዩ ዐ/ህግ ይግባኝ ባዩ በዐ/ህጉ ምስክሮች

ለተመሰከረባቸው ምስክርነት በመ/ምስክሮች ስላላስተባበሉ የተጣለባቸው የ13 ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት የሚያንስ እንጂ የሚበዛቸው አይደለም ለሚለውም

## 1.7 ያቀረቡዋቸው የቅጣት ማቅለያ

ሃሳብም በወ/መ/ሕግ የተሸፈኑ አይደሉም

## 1.8 በይግባኝ ባይ የስር ፍ/ቤት ከወንጀሉ ክብደት አንፃር ለሰጠው ፈርድ ተገቢ

በመሆኑ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የፍርድ ውሳኔው እንዲያፀድቀው የሚል ነው::

1.9. መልስ፣ በተራ ቊጥር 1.6 - ስለተሰጠው መቃወሚያ በመሰረቱ ይግባኝ ባዩ ለተመሰከረባቸው ምስክርነት አላስተባበሉም ለሚባለው በዚሁ ጉዳይ አቃቤ ህጉ ካቀረባቸው ምስክሮች በይበልጥ የመከላከያ ምስክሮች በማቅረብ ለተሰጠው የዐ/ህግ ምስክርነት ያፈረስኩት ለመሆኔ በ1ኛው ደረጃ የስር ፍ/ቤቱ በመከላከሉ ሂደት የተከናወነውን ጥረትና ድካም በጉልህ እያስረዳ አላስተባበለምና የተጣለበትን የ13 ዓመት ቅጣት የሚያንሰው ነው የሚያሰኝ አይሆንም:: ምክንያቱም በሚገባ ተከላክያለሁና ነው::

1.20 - መልስ በተራ ቁጥር 1.7 - ስለቀረበው መቃወሚያ፣ ይግባኝ ባዩ ያቀረቡዋቸው የማቅለያ ሃሳቦች በህግ በኩል ተቀባይነት የለውም የሚያሰኝ ምክንያት ውጤት አይኖረውም:: ምክንያቱም የወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁጥር 185/ለ/ በተደነገገው መሰረት ፍ/ቤቱ የአንድ ተከሳሽ የሚያቀርበውን የቅጣት ሃሳቦችን በመመልከትና እግምት ውስጥ አስገብቶ ቅጣቱን ዝቅ አድርጎ መቅጣት የሚችል መሆኑን በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁጥር 185/ለ/ በተመለከተው መሰረት ለፍ/ቤቶች ስልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ህጉ ያስረዳል::

ታድያ የልዩ ዐ/ህግ የመጀመሪያ ስር ፍ/ቤቱ የቀረበውን ማቅለያ ያለመቀበሉን ትክክል ነው ማለታቸውን አግባብነት የለውም:: የስር ፍ/ቤቱ እኔ ያቀረብኩዋቸውን አሳማኝና ትክክለኛ የሆኑ የቅጣት ማቅለያ ፅሑፌ/ሃሳቤን/ አልቀበለውም ብሎ ውድቅ ቢያደርገውም ሌሎች ተከሳሾች ከእኔ በኋላ የተፈረዱትን እንደኔ አይነቱ ተመሳሳይነት ያለውን የቅጣት ማቅለያ ያቀረቡትን ተቀብሎ ዝቅ አድርጎ ሲቀጣ ታይተዋል:: ታድያ በህጉ አሰራር ሂደት በእኔ በኩል ስመለከተው በጉልህ ሚዛናውነቱን የሳተ ነው እላለሁ::

1.21 - መልስ በተራ ቊጥር 1.18 - በተገለፀው መቃወሚያ በተመለከተ፣ የልዩ ዐ/ህግ የስር ፍ/ቤቱ የሰጠውን ፈርድ የሚያንስ እንጂ የሚበዛ አይደለም:: ስለዚህ የፍርድ አሰጣጡ ትክክለኛ ነው:: ለተባለውም አባሉ ትክክለኛ ከሰብአዊ መብት አመለካከት አንፃር ሲመዘን ፍትሃዊነት የተላበሰ አባባል ባለመሆኑ ክቡር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የልዩ ዐ/ህግ ተቃውሞ ውድቅ ያደርግልኛል የሚል የፀና እምነት አለኝ:: ይኸውም በልዩ ዐ/ህግ ቀርበው የሰጡትን ምስክርነት አኳያ እኔ ያቀረብኩዋችው መ/ምስክሮች የሰጡትን ቃል በይበልጥ ተአመኝነት ስላለው ነው::

1191

3ኛ/ ይግባኝ ባይ የፖለቲካ እስረኛ መርማሪ በመባል የቀረበው ማስረጃ ያልተደገፈ ነው:: በሙያ መምህር ነኝ በማለት ተከራክረዋል::

- መልስ ሰጪው መምህር አልነበርኩም አላለም ነገር ግን ሟቹን ምርመራ ክፍል ውስጥ አስገብተው መርምረዋል:: ይህም በማስረጃ ተረጋግጠዋል:: የይግባኝ ባይ ክርክር ለመፈፀማቸው ከተረጋገጠው ወንጀል ጋር አግባብነት የለውም:: ስለዚህም ውድቅ እንዲሆን እንጠይቃለን ሲል በመቃወሚያው ገፅ ሁለት/2/ ላይ ዘርዝሮ አቅርቦታል::

## 1ኛ ደረጃ የመቃወሚያ መልስ

1.1. በመሰረቱ እኔ የመልስ መቃወሚያ አቅራቢ ምድብ ስራዩ ተራ የመንግስት ሰራተኛ /አስተማሪ/ እንጂ የፖለቲካ እስረኞች መርማሪ አይደለሁም፣ አልነበርኩምም፣

1.2. ከላይ እስከታች በሚገኙት የወቅቱ መንግስት ሃላፊዎች በቁርኝትና በመተሳሰር የፖለቲካ ትስስሩን ለማፈራረስ ሲል ከወረደው አስተዳዳሪ ከነበረውና ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን የህወሃት አባል አሳድረሃል በማለት በምርመራ ሟች አቶ ገ/እግዚአብሄር ኪዳኑን በመደብደብ አስከሬኑ በበርሃ እንዲቀበር አላደረግኩም:: ይኸውም በደርግ ዘመን መንግስት ይህን ለማድረግ ምንም የፖለቲካና የመንግስት ስልጣንና ተግባር አልነበረኝም::

1.3. እኔ ተራ መምህር በፈቃዱ ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤት ቢሮ ድረስ ተገኝቼ የሰው ልጅን ለመደብደብና ለመመርመር የሚያስችል አንዳችም የስልጣን ሃላፊነት አልነበረኝም:: ይህ በዓቃቤ ህግ የቀረበብኝ ክስ ህግን ማእከል ያላደረገ በግለሰብ ቂም በቀል የቀረበ ጥቆማ መሆኑን እገልፃለሁ::

## 1.2 መልስ ሰጪው የልዩ ዓቃቤ ህግ ሶስት
## የሰው ማስረጃዎች አቅርቤ አስመስክሬበታለሁ ስለሚለው
## 2ኛ ደረጃ የመቃወሚያ መልስ

1.1. የልዩ ዐቃቤ ህግ እነ ለማ ሃይለ 3/ሶስት/ ቁጥር ግለሰቦች በማስረጃነት አቅርቦ የነበረ ቢሆንም እኔ ከላይ እንደገለፅኩት መምህር እንጂ የፖለቲካ እስረኞች መርማሪ አለመሆኔን እየታወቀ እነዚህ ምስክሮች በወቅቱ ከእነ I አለቃ አባይ ገ/ህይወት ከወረዳው አስተዳደር ቢሮ ውስጥ ሲገቡ ነበር በማለት ከእውነት በራቀ ሁኔታ ተናገሩ እንጂ በማይመለከተኝ ስራ ለመግባትና ይህንኑ ስራ ለመፈፀም የሚያስችለኝ የስራ ደረጃና ሃላፊነት አልነበረኝም ወደ ቢሮ ውስጥም አልገባሁም::

1.2. ሟቹን በማን ተመረመረ? በምን አይነት የመግረፍያ መሳሪያ ተገርፎ ለሞት ተዳረገ የሚሉትን መሰረታዊ ነጥቦች ሳይሟሉ ተከሳሹ ወደ ቢሮ ሲገባ አየነው በሚለው ቃል ብቻ የወንጀሉ ሁኔታ ተከናውነዋል የሚያስችል አንዳችም ውጤት አላስገኘም፣ አባባላቸውም ውሸት ነው::

1.3. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ወደ ፍርድ ሒደትም ሆነ ወደ መከላከሉ ደረጃ የሚያስገባ ነጥብ የሌለው መሆኑ እየተገነዘበ እንድከላከል ብሎ መወሰኑና የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ መስጠቱ የህግ ስህተት እንዳለው ከመዝገቡ ሂደት አኳያ አይቶ ለመረዳት የሚቻል ይመስለኛል::

1.4. እንዲያው የ1ኛው ደረጃ ፍ/ቤት እኔ ተከሳሽ መከላከሉ ሳያስፈልገኝ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ ቊጥር 141 መሰረት በነፃ ማሰናበት እየተገባው የእኔ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቴን በመንፈግ የፍርድ ውሳኔ መስጠቱን የተከበረው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በልዩ ዐ/ህግ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ እንድያደርግልኝ በአፅንኦት አመለክታለሁ::

## 1.2 የልዩ ዐ/ህግ በመቃወሚያ መልሱ
## እኔ ባቀረብኩዋቸው መ/ምስክሮች
## እርስ በራሱ የሚጋጭ ነው ብሎ ላቀረበው ተቃውሞ
## 3ኛ ደረጃ መቃወሚያ መልስ በተመለከተ

1193

1.1. ሟች አቶ ገ/እግዚአብሄር ኪዳኑ ምርመራ በተካሄደበት የአስተዳደር ቢሮ ሲገቡ እኔ በቦታው እንዳልነበርኩና ሟቹን ወደ ምርመራ ክፍል ለማ ሃይለ የተባለው የልዩ ዐ/ህግ ምስክር የነበረው ሬሳ ይዞት ሲገባ በዚህ ግዜ እኔ ከመምህርነት ስራ ውጭ ሌላ የስልጣን ክልልና ሓላፍነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
*THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*
*FEDERAL SUPREME COURT*

ቀን Date 8-7-96
ቁጥር Ref. No. 11826

ለ- [illegible]
[illegible]

በይግባኝ ባይ [illegible] እና
በመልስ ሰጭ [illegible] መካከል ባለው
የወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ወ/ችሎት 7-8 ቀን
1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት [illegible] ሰጥቷል::
ስለዚህ [illegible] ትክክል ግልባጭ 2 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር
አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን::

9-7-96

ሐብታሙ ወርቁ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ም/ሬጅስትራር

1195

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
FEDERAL SUPREME COURT

ቀን 8-7-96
Date
ቁጥር 11826
Ref. No.

ለ- [illegible]
[illegible]

በይግባኝ ባይ [illegible] እና
በመልስ ሰጭ [illegible] መካከል ባለው
[illegible] ወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት
ወ/ችሎት 7-8 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ይግባኙን
ባለመቀበል [illegible] የሰጠ ስለሆነ የ[illegible] ትክክል ግልባጭ
2 ገጽ በእናንተ በኩል ለይግባኝ ባዩ እንዲደርሰው እንገልፃለን።

8/7/96

ሐብታሙ ወርቁ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ም/ሬጅስትራር

1196